# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረምረቃ መርሐ ግብር


**በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሠገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ**


በ

በረከት ሁሴን



ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሠገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍፊት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ


## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድህረምረቃ መርሐ ግብር

ለበተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

በረከት ሁሴን


ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረምረቃ መርሐ ግብር

**በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሠገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍፊት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ**

**በ**

**በረከት ሁሴን**

**ነሐሴ 2010**

የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ______________________ | ______________________ |
| **የፈታኞች ስም** | **ፊርማ** |
| ______________________ | ______________________ |
| ______________________ | ______________________ |

## ምስጋና

በመጀመሪያ ስለሆነው ሁሉ እግዚአብሔር ይመስገን። ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጠቃሚ ሙያዊ አስተያየትና ድጋፍ እንዲሁም አባታዊ ምክር ለለገሱኝ ለመምህሬና ለአማካሪዬ ለረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ ገብሬ ከፍተኛ የሆነ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለእኔ እዚህ ደረጃ መድረስ ቅን ሀሳባቸውና ድጋፋቸው ላልተለየኝ ቤተሰቦቼ፣ ለአክሊሉ፣ ለዘቢባና ለብርሃኔ እንዲሁም ለጓደኞቼ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናት ጽሁፌን በተሳካ መልኩ እንዳከናውን የገንዘብ እገዛ ስላደረገልኝ አመሰግናለሁ።

ለስራዬ መሳካት ትብብር ላደረጉልኝ ለሠገን 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት መምህራንና ለጻፈችልኝ ሰአዳ ምስጋናዬ ወደር የለውም።

# ማ ው ጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........ i

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ iv

አጠቃሎ ........ v

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱዳራ ........ 1

1.2. አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 4

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4

1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 4

ምዕራፍ ሁለት

ክለሣ ድርሳን ........ 5

2.1. የንባብ ምንነት ........ 5

2.2. አንብቦ የመረዳት ምንነት ........ 6

2.3. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች ባህሪያት ........ 9

2.4. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች ........ 14

2.5.የንባብ ፍጥነት ምንነት ........ 15

2.6. የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ........ 16

2.7. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 19

ምዕራፍ ሦስት

የአጠናን ዘዴ ........ 20

3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 20

3.2. ተጠኚዎችና የናሙና አወሳሰድ ........ 20

3.2.1የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 20

3.2.2.የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 21

3.2.3.የተማሪዎች አመራረጥ ....................................................................................21
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ..................................................................................21
3.4. የመረጃ አሰባሰብ ..........................................................................................................23
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ................................................................................................23
ምዕራፍ አራት
የመረጃ ትንተና .............................................................................................................24
4.1. የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች ..........................................................................24
4.1.1የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና አንድ አንጻር ..............................................25
4.1.2የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና ሁለት አንጻር ..............................................26
4.1.3.የተጠኚ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ........................................27
4.2. የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና ፈተና ሁለት ዝርዝር መረጃ ....................................28
4.2.1የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ ...........................................................29
4.2.2የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት ...........................................................30
4.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ጋር ያለው ግንኙነት ....................................................................................................................34
4.4. የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ግንኙነት .......................................35
4.5. የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ግንኙነት .......................................36
4.6. በንባብ ፍጥነትና በአንብቦ የመረዳት መካከል ያለው ተዛምዶ ..................................37
4.7. ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..........................................38
ምዕራፍ አምስት ...............................................................................................................41
ማጠቃለያና አስተያየት ....................................................................................................41
5.1. ማጠቃለያ ...................................................................................................................41
5.2. አስተያየት ...................................................................................................................42
ዋቢዎች ..........................................................................................................................44

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ሠንጠረዥ 1፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አንድ ውጤት .................................... 25

ሠንጠረዥ 2፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት ውጤት .....................................26

ሠንጠረዥ 3፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ የሚያሳይ ...........................................27

ሠንጠረዥ 4፡ የተጠኝዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ ...........................................29

ሠንጠረዥ 5፡ የተጠኝዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት .........................................31

ሠንጠረዥ 6፡ የተጠኚዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት የሚያሳይ መረጃ ...........................32

ሠንጠረዥ 7 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከንባብ ፍጥነትና ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ግንኙነት .......................................................................34

ሠንጠረዥ 8፡ ንባብ ፍጥነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ...........................................................................................37

ሠንጠረዥ 9፣ ለቃለ መጠይቁ የተሳተፉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ ........................38

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በደቡብ ብሄሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሠገን 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህም የሠገን 2ኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ እንዲሁም በናሙናነት ከተመረጠው ትምህርት ቤት ከሚማሩት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል አማርኛ ኢአፍ ፈት የሆኑ 100 ተማሪዎች በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው የፍጥነት ንባብ መለኪያና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና በመፈተን፣ ለዘጠነኛ ክፍል አማርኛን በማስተማር ላይ ለሚገኙ መምህራን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በፈተናና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ በተጠቀሱት የመረጃ ማሰባሰቢያ የተገኙት መረጃዎች ተጠናቅረው በመጠናዊ ገላጭ የምርምር ዘዴና እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ የአይነታዊ ምርምር ዘዴ በሆነው በገላጭ የአተናተን ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን እና የንባብ ፍጥነትን ተዛምዶ በ SPSS የኮምፒውተር ፕሮግራም ተሰልቷል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደሆነና የንባብ ፍጥነታቸውም ዘግተኛ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡ በዚህም በአንብቦ የመረዳት ችሎታ እና በንባብ ፍጥነት መካከል ተዛምዶ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ለተማሪዎቹ በፍጥነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን የሚከተሉት ምክንያቶች ተጠቅሰዋል፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ጀምረው ቋንቋውን ተምረው መሠረት ይዞ አለመምጣት፣ ለቋንቋ ትምህርቱ ትኩረት አለመስጠትና ተማሪው የንባብ ክሂሉን ለማዳበር የሚያደርገው ጥረት አለመኖር ናቸው፡፡ በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች በመመርኮዝ የንባብ ፍጥነትን ለማሻሻልና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር መምህራን ተማሪዎች የንባብ ልማዳቸውን እንዲያጎለብቱ ቤተ መጻሕፍት ገብተው እንዲያነቡ ቢያበረታቷቸው፣የተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ የመረዳት እና የንባብ ፍጥነት ለማሻሻል በየጊዜው እየለኩ ድጋፍ ቢያደርጉና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ ስላልሆነ የሚስተካከልበት ሁኔታ ቢፈጠር የሚሉ ጠቃሚ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱዳራ

የንባብ ባህል ከትምህርት መስፋፋትና ማደግ ጋር የማይነጣጠል ትስስር አለው፡፡ በሐገራችን በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዋና ዋና አላማዎች አንዱ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ማዳበር ነው፡፡ የማንበብ ክሂል ማዳበር ለማዳመጥ፣ ለመናገርና ለመፃፍ ክሂሎች መዳበር አስተዋጽኦ እንዳለው Sheng (2000:12) ያብራራሉ፡፡

የማንበብ ክሂል በውስጡ በርካታ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ይይዛል፡፡ ከነዚህም አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲሆን የፍጥነት ንባብም እንደዚሁ ነው፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የፍጥነት ንባብን በተመለከተ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የፍጥነት ንባብ ክሂል ተያይዥ በሆነ መልኩ በአንድ ላይ መዳበር እንዳለባቸው እና በሽምደዳ የሚካሄድ የፍጥነት ንባብም ሆነ ከተገቢው ጊዜ በላይ የሚወስድ አንብቦ የመረዳት ሂደት እንደማይደገፉ Anderson ( 1999:29) ይገልጻሉ፡፡ የቋንቋ ተማሪዎች እነዚህን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች እንዲያሻሽሉ ማድረግ እንደሚቻልም ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ንኡሳን ክሂሎች በአንድነት ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡

በሌላ በኩል የአንባቢዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት በተመለከተ Fry (1963:52) ሲገልጹ ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸው እንዲጨምር ደግሞ ብዙ ማንበብ፣ ጭምቅ ሀሳብ የያዙ ጽሁፎችን ማንበብ፣ የመረዳት ችሎታን ለመጨመር የሚያስችሉ ሳቢ ጽሑፎችን አዘውትረው ማንበብ፣ ለብዙ ጊዜ የማንበብ ልምድን ማካበት፣ ፍጥነትን በራስ ወስኖ ለማንበብ መዘጋጀትንና በንባብ ጊዜ ለሚነበቡ ምንባብ ትኩረት የመስጠት ልምድን ማካበት ይኖርባቸዋል በማለት ያብራራሉ፡፡

የንባብ ክሂል ቋንቋን በማስተማር ሂደት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የዚህ ክሂል በአግባቡ መዳበር ለሌሎች ክሂሎች ማደግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ የተሻለ እና ጥሩ አንባቢ ለመሆን የዳበረ

የንባብ ችሎታ ያለው መሆን ያስፈልጋል፡፡ የንባብ ችሎታ ሲባል በንባብ ሂደት የምንጠቀምባቸው የተለያዩ የአነባበብ ስልቶች እና የንባብ ፍጥነታችንን ያጠቃልላል፡፡ የዳበረ የሚባለው የንባብ ችሎታም በተገቢው ፍጥነት አንብቦ መረዳትን የሚመለከት ነው (Nuttal 1982:3)፡፡ ከዚህ የምንረዳው አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት መገንዘብ ሲሆን በፍጥነት ማንበበብ ለአንብቦ መረዳት አስተዋጽኦ እንዳለው ነው፡፡

በ2009 ዓ.ም በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልላዊ መንግስት ከ1ኛ- 8ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና ከተዘጋጀው ማንዋል የምናገኘው መረጃ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል፡፡

> ትምህርት ሚኒስቴር (2007፡ 7) በማንዋሉ እንደገለጸው በኢትዮጵያ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለማዳረስ ስኬታማ ስራ ቢሰራም በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ እርከን የሚማሩ ተማሪዎች የንባብ ችሎታ ግን አስደንጋጭ መሆኑን የEGRA ጥናት ውጤት አመልክትዋል፡፡ የዝቅተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ምዘና ጥናት ደቡብ ክልልን ጨምሮ በስምንት ክልሎች የተካሄደ ሲሆን የማንበብ ችሎታን በተመለከተ ሰባት ቁልፍ ዘርፎችን ገምግሟል፡፡ እነሱም በ2ኛና በ3ኛ ክፍል ፊደላትን የመለየት ዕውቀት፣ የንግግር ድምጾች ግንዛቤ፣ የፊደልና የድምጽ ግንኙነት ዕውቀት፣ ተዘውታሪ ቃላትንና አዳዲስ ቃላትን ማንበብ፣ ድምጽ በማሰማት አቀላጥፎ የማንበብ ግንዛቤና አዳምጦ የመረዳት ችሎታ ናቸው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው 2ኛ ክፍልን ከአጠናቀቁ ተማሪዎች መካከል 34% አንድም ቃል ማንበብ ያልቻሉ ሲሆን የ3ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ከአጠናቀቁ ተማሪዎች መካከል 20% የሚሆኑ ምንም ቃል ማንበብ ያልቻሉ ሲሆን 30% ደግሞ በአንብቦ መረዳት ምዘና ምንም ውጤት እንዳላስመዘገቡ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ ተዘውታሪ ቃላትን በማንበብ ረገድም የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች በደቂቃ 20 ቃላትን፣ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች በደቂቃ 29.4 ቃላትን ማንበብ መቻላቸውን ጥናቱ አመልክቷል፡፡

በመሆኑም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## 1.2. አነሳሽ ምክንያት

ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ የንባብ ችሎታን ማዳበር እንደሆነ ከላይ ተገልጾአል፡፡ የንባብ ችሎታ ስንል ደግሞ በተገቢ ፍጥነት ማንበብ እና አንብቦ መረዳትን ይመለከታል፡፡ በአገራችን በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በርካታ የሀገራችን ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ደካማ እንደሆነ ነው፡፡ መኮንን ( 2000) "በአዊኛ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ የመረዳት ችሎታ ግምገማ" በሚል ርዕስ እንዲሁም ተሾመ ( 1997) "በከንባታ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት" በሚል ርዕስ አያሌው (2001) "በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንብቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ፡- በወልዲያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ ጥናት" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት ባደረጉት ጥናት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ አሁንም ትልቅ ችግር እንደሆነ አመላክቷል፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑ በየጊዜው በወላጆች፣ በመምህራን፣ በተማሪዎችና በተለያዩ አጥኚዎች ይነገራል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የሚነበበው ጽሁፍ ሳቢና ተመጣጣኝ አለመሆን፣ የተመደበው ክፍለጊዜ አናሳ መሆን፣ የተማሪ ቁጥር መብዛትና የመምህሩ አተገባበር በአደናቃፊነት ተዘርዝረዋል፡፡ እስከ አሁን በተለያዩ ጥናቶች እነዚህ ጉዳዮች ቢነሱም አሁንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፈ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም በተማሪዎች የንባብ ችሎታና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል በጥናት ማረጋገጥ ለመማር ማስተማሩ ውጤታማነት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑና በተጨማሪም አጥኚዋ በሠገን 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ባስተማረችበት አስር አመታት ዘጠነኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የሚያስመዘግቡት ውጤት ዝቅተኛ መሆኑ የምንባብ ፈተና ላይ የሰአት አጠቃቀም ችግር ማስተዋሏ ጥናቱን ለማካሄድ አነሳስቷታል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሰገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ኢአፍፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው። ጥናቱ ከዋናው ዓላማ በመነሳት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

1. የአንብቦ መረዳት ችሎታን መመርመር
2. የንባብ ፍጥነት መመርመር
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

በዚህ መሠረት፡-

1. የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል መምህራን ምን እገዛ ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ ያሳያል።
2. የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ይጠቁማል።
3. በዚህ ርእስ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በሠገን አካባቢ ህዝቦች ዞን በሰገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ኢአፍፈት ተማሪዎችን በናሙናነት በመውሰድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው። ከዚህ ውጪ የንባብ ክሂል ትምህርት አተገባበርን፣ የንባብ ክሂል የማስማተር ስነዘዴን፣ ለንባብ ክሂል ማስተማሪያነት የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አይመለከትም።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሣ ድርሳን

### 2.1. የንባብ ምንነት

ማንበብ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይበልጥ አስፈላጊና መሰረታዊ ከሆኑት ክሂሎች ውስጥ አንዱ መሆኑን Lindsay and Knight (2006:70-71) ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም ንባብ በማንኛውም ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች እጅግ አስፈላጊ የሆነ ክሂል ነው፡፡ ”የተማሪዎች ስኬትም ሆነ ውድቀት የሚወሰነው በሚኖራቸው የግል የማንበብ ክህሎት ወይም ችሎታ ነው፡፡” በማለት Nelson (1963: 18) ያስረዳሉ፡፡ “ንባብ በአንድ ጽሁፍ አማካኝነት የሰፈረውን መልእክት መረዳትና ማገናዘብን ይመለከታል፡፡ እንዲህ ስለተባለ ግን መልእክቱ በጽሁፍ አማካኝነት በቀላሉ ሰፍሮ የሚገኝ አለመሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ የሰፈረውን መልእክትም ለመረዳት የአንባቢን ንቁ የአእምሮ ተሳትፎ ይጠይቃል” በማለት አለም /1997፣2/ ይገልፃሉ፡፡

ስለንባብ ምንነት Alderson (2000:3) እንደገለፁት፣ ንባብ ከተፃፈ ጽሁፍ ላይ መረጃ መውሰድ ብቻ ነው ብሎ ወስኖ መግለጽ ያስቸግራል፡፡ ይኸውም አንድ አንባቢ የሚያነበው ለተለያየ ዓላማ ነው፤ በመሆኑም ከዓላማው አንፃር የተለያዩ ውህድ ክሂሎችንና ስትራቴጂዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ ስለዚህ ንባብ ለእውቀት /ለመረዳት/ ተብሎ ብቻ የሚተገበር ሳይሆን እንደ አንባቢው ዓላማ ለተለያዩ ተግባራት የሚከወን በመሆኑ በውስጡ ሌሎች ንኡሳን ክሂሎችን አካቶ የያዘ ችሎታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአንባቢውን የቋንቋ ብቃት የሚለካ ክሂል ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ May (1990፡10) አገላለፅ የንባብ ምንነት ከተለያዩ ነጥቦች አንፃር ሊገለጽ ይችላል፡፡ ይኸውም፡-

- ንባብ በጽሁፍ የቀረበውን ሀሳብ የመረዳት ሂደት ነው፡፡
- ንባብ የመተርጎም፣ ፍቺ የማፈላለግና በጽሁፍና በስዕል የቀረቡ መልዕክቶችን ወደ ግል ግንዛቤ የመተርጎም ሂደት ነው፡፡
- ንባብ አንባቢው በጽሁፍ ከቀረቡ ቃላት ጋር የሚያደርገው ጭውውትም ሊሆን ይችላል፡፡ ማለትም አንድ ጽሁፍ ለመረዳት በሚደረግ ሂደት አንባቢ ከቃላት ጋር በመነጋገር

በመጨዋወት የጸሐፊው ሀሳብ ይህ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም Grellet (1981፡8) “ንባብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከር፣ ራስን ጥያቄ መጠየቅንና ንቁ ተሳትፎ ማድረግን የሚፈልግ ሂደት ነው፡፡” በሂደቱም አንባቢ ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላት ፍቺዎችን የሚገምትበት ገና ከመነሻው በአገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደ ፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት፣ ያነበበውን ፅሁፍ መረዳት አለመረዳቱን ራሱን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሆኑን እንረዳለን በሌላ በኩል የተለያዩ ምንባቦችን ሲያነብ የተለያዩ ችሎታዎችንና ስልቶችን መጠቀም እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡

በአጠቃላይ ስለንባብ ምሁራን ወጥ የሆነ ብያኔ ያልሰጡበት ምክንያት ከንባብ ባህሪ የመነጨ እንደሆነ Alderson and Urguhart (1984፡1) ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም የንባብ ትግበራ ግላዊና ረቂቅ መሆኑ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው የተለያዩ አንባቢዎች አንዱን ጽሁፍ የሚረዱበት መንገድ፣ የሚያነቡበት ዓላማና የአነባበብ ዘዴያቸው የተለያየ መሆን ነው፡፡ ንባብ ማለት ለአንዱ የሚፈለገውን መረጃ ብቻ ነቅሶ ማውጣት ሲሆን ለሌላው ደግሞ መልዕክቱን በዝርዝር መገንዘብ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ንባብ ጸሀፊው ላስተላለፈው መልዕክት አንባቢ ምላሽ የሚሰጥበት ተግባር የሚሆንበት ሂደትም አለ፡፡

## 2.2. አንብቦ የመረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት የምንለው አንባቢው በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ፍንጭ አመላካቾችን በመጠቀም መልዕክቱን የሚቀበልበትን እና ግንዛቤውን የሚያዳብርበትን ሂደት ነው፡፡ Williams (1984፡15)፡፡ ይህም አዲሱን ጹሁፋዊ መልዕክት ቀደም ሲል አዕምሮ ውስጥ ከነበረው ሀሳብ ጋር በማዛመድ እየገመገመ የሚቀበልበት ወይም አዲስ አዕምሮአዊ ምስል የሚከሰትበት ነው፡፡ በሂደቱም ቀደም ሲል በነበረው ግንዛቤ መሰረት ከጽሁፉ አገኛለሁ ብሎ የገመተው ነገር ትክክል ስለመሆን አለመሆኑ እያረጋገጠ ወይም እያስተካከለ ግንዛቤውን ያሰፋል፡፡ ይህን ማድረግም የቃላትን ፍቺ፣ ሰዋስዋዊ አያያዦችን፣ የሀሳብ አደረጃጀትን መገንዘብ እና በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ የቀረቡ ወይም ያልቀረቡ ነጥቦችን መለየት እና የተገኘውን መልዕክት ከቀደመ ዕውቀት ጋር እያቀናጁ የመገንዘብ ችሎታ የሚጠይቅ ነውና ሊያዳብረው ይገባል Lage (1981፡444)፡፡

ንባብ ውስብስብ ሂደት ሲሆን አንብቦ መረዳት ደግሞ አንዱ የንባብ ችሎታ መገለጫ ነው፡፡ Perfetti (1985:9) ሲገልፁ “ንባብ የበርካታ አእምሮአዊ ሂደት ውጤት ነው፡፡ በተለይም

መረዳት በአእምሮታዊ ተግባር ውስጥ፣ ማንበብ የሚወሰነው በአንባቢው እውቀትና የሚነበበውን ነገር ከመረዳት ጋር የተያያዘ ነው።" ሲሉ፣ Grellet (1996:147) ደግሞ አንብቦ መረዳት ስንል፣ አንድን ጽሁፍ ቴክስት የያዘውን መልእክት በአግባቡ መርምሮ መገንዘብ መቻል ማለት ነው፤ የምናነበው ነገር ደግሞ ማስታወቂያ፣ የጋዜጣ ርእስ አንቀጽ፣ የሳይንሳዊ ጆርናል መጣጥፍ ወዘተ ሊሆን ይችላል በማለት ያብራራሉ።

እንደ Greenwood (1981፡89) አገላለጽ አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መገንዘብ ነው። በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ያለን መልዕክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ማወቅ የግድ አይሆንም። በጽሁፍ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክትና መልዕክቱን ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ጉዳዮች መረዳት ግን ወሳኝ ነው። ይህም ሲባል አንባቢ በግልጽ የተቀመጠው መልዕክት ላይ ብቻ ወስኖ መቅረብ አለበት ማለት ሳይሆን በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት መነሻ በማድረግ በመመርመር የሚደርስበትን ስውር መልዕክትም መረዳት ይጠበቅበታል። በዚህን ጊዜ ከጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ አገልግሎት እና ፍቺ መረዳት የግድ ነው። በተጨማሪም የምንባቡን ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለፅ በጽሁፍ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርስ በርስ ቁርኝት መረዳት ተገቢ ነው።

አንብቦ መረዳት የአንድ ጽሁፍ ቅደም ተከተላዊ የሃሰብ አገላለጽ የመጀመሪያው ዐርፍተነገር ከቀጣዩ ጋር ያለውን የሀሳብ ግንኙነትና ግጥምጥምነት የሚከውኑ አያያዦች የፀሐፊው ሀሳብ የሚንፀባረቅባቸው በመሆናቸው ሊተኮርባቸው የሚገቡ ናቸው። Nuttal (2000: 28) አንብቦ መረዳት ማለት በአንድ በቀረበ ጽሁፍ ወይንም ምንባብ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ መረጃዎችን መገንዘብ ማለት ነው። በእርግጥ የአንብቦ መረዳት ደረጃ ሊለያይ ይችላል። ይህም ከሚነበበው ነገር ከሚነበብበት ዓላማ ከአነባበብ ዘዴው መለያየት ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ አንድ ማስታወቂያና አንድ ሳይንሳዊ ጥናት በተመሳሳይ መንገድ አይነበብም። የማስታወቂያው መልዕክት በገረፍታ ሊደረስበት ሲቻል የሳይንሳዊን መልዕክት ለመረዳት ግን ጥልቅ ንባብ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ስለ አንብቦ መረዳት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ቢሰጡም አብዛኞቹ ግን አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ያለን ሀሳብ መገንዘብ መቻል መሆኑን ይስማማሉ።

ምንአልባት የእያንዳንዱ አንባቢ የአረዳድ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ነገርግን አንድ ሰው የሚፈልገውን መረጃ አንብቦ መገንዘብ ከቻለ አንብቦ መረዳት ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

Sheng (2000፡13-15) አንብቦ የመረዳት ተግባርን በሁለት መልኩ ከፍለው ያብራራሉ፡፡ የመጀመሪያው በሚቀርበው ምንባብ ውስጥ በግልጽ የቀረቡ መልእክቶችን ያለ ምንም ልፋት አንብቦ መረዳትን የሚያመላክት ሲሆን በጽሑፍ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና መልእክቶች መገንዘብን፣ በግልጽ የተቀመጡ ሁነቶችን፣ ድርጊቶችን፣ ክስተቶችን፣ ወዘተ. ቅደም ተከተል ማስታወስን፣ በጽሑፍ ውስጥ ያለምንም ማሻማት በግልጽ የሰፈሩ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን መለየት መቻልን፣ የምክንያትና ውጤት ትስስርን ማስታወስን፣ ወዘተ የሚገልጽ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ያለው የአንብቦ መረዳት ተግባር ደግሞ ተማሪዎች ተጠየቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በጽሑፍ ውስጥ ግልጽ በሆነ መልኩ ያልተቀመጡ ሀሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ የሚጠቁም ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደግሞ በግልጽ ከሚታዩት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መለየትን፣ ፍሬ ሀሳቡን ወይም ጭብጡን መለየትን፣ ደጋፊ ሀሳቦችን ለይቶ ማወቅን፣ በምክንያትና ውጤት ትስስር የተነሳ ተከትሎ ሊመጣ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ነገር መገመትን፣ በጽሑፍ ውስጥ ግልጽ በሆነ መልኩ የተቀመጠውን መነሻ ሀሳብ በፍንጭነት በመጠቀም የገፀ-ባህሪያትን ባህሪ መገንዘብን፣ ፀሀፊው የተጠቀመበትን ቋንቋ ፍች በትክክል መለየትን፣ ወዘተ የሚመለከት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአንብቦ መረዳት ንዑስ ክሂል ቃላትና ሐረጋትን የመረዳት ክሂል ነው፡፡ የቃላትና የሐረጋትን ትርጉም በጽሑፍ ውስጥ በግልጽ ከሰፈሩ መረጃዎችና ፍንጮች በመነሳት ወይም ከቀደመ እውቀት በመነሳት ወይም ሁለቱን በማቀናጀት የመረዳት አቅምን የማጎልበት ሂደት ነው፡፡ ለዚህም የቃላትና የሐረጋትን ቀጥተኛ ትርጉም ከመረዳት ባሻገር አውዳዊ ፍቻቸውንም መረዳት ይጠበቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለአንብቦ መረዳት መሠረታዊ የሆኑትን ፈሊጦች፣ ዘይቤዎችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ከገቡበት አውድ አንጻር መተርጎምና መረዳትም ትልቁ ክህሎት ነው፡፡

ሌላው የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች የንባብ ስልቶች ሲሆኑ፣ እነዚህም የገረፍታ ንባብ፣ የአሰሳ ንባብና ጥልቅ ንባብ የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህን ስልቶች ጠንቅቆ በማወቅ በንባብ ጊዜ እንደ አላማችን በመቀያየር የመጠቀም ልምድን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው አንብቦ መረዳት የመገንዘብና የማስታወስ ሂደትን ማለትም ከአነበቡት ጽሁፍ ውስጥ መልዕክትን ማወቅንና በግልጽ የተቀመጡና

ያልተቀመጡ አገላለጾችን መረዳት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አንብቦ በመረዳት ሂደት ለእነዚህ ንኡሳን ክሂሎች ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## 2.3. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፈተናዎች ባህሪያት

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ምንባቡ ከቀረበበት ቋንቋ ጠንከር የሚል መሆን የለበትም፡፡ ከምንባቡ የሚወጡ ጥያቄዎች ግልጽና ቀላል በሆነ ቋንቋ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመፈተን የሚቀርቡ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ አለባቸው፡፡

እንደ አለም (1995፡12-13) አገላለጽ የአንብቦ መረዳትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎች በጽሁፍ ወይም በቃል ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ አቀራረባቸውም አጭር መልስ እንዲሰጡ በማድረግ፣ በክፍት አጠያየቅ፣ በምርጫ ወይም በእውነት ሐሰት በል በሚል መልኩ ሊሆን ይችላል፡፡ ጥያቄዎቹ የሚቀርቡበት መንገድ የተለያየ ሊሆን ቢችልም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ግን ግብ መቺ መሆን እንዲችሉ ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

1. ጥያቄዎቹ ምንባቡን ባላነበበ ሰው ሊመለሱ የሚችሉ ሊሆን አይገባም፡፡
2. ጥያቄዎቹ በአንድ በተወሰነ የምንባቡ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ ሁሉንም የምንባቡን ክፍል በሚዳስሱበት መንገድ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ሊመረመር ይገባል፡፡
3. የጥያቄዎቹ ቁጥር እጅግም ሳይበዛ እጅግም ሳያንስ በቂ የሆነ መጠን እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡
4. የተለያዩ የአንብቦ መረዳት መልመጃ የማቅረቢያ መንገዶች አሉ፡፡ ስለዚህም ጥያቄዎቹን በተለያየ አቀራረብ መንገድ ለማቅረብ መሞከር አስፈላጊ ይሆናል፡፡
5. ጥያቄዎቹ አንድ አንባቢ ሊኖረው ከሚገባው የንባብ ስትራቴጂ ጋር የማስተዋወቅ ባህል ሊኖራቸው ይገባል፡፡
6. ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
7. ጥያቄዎቹ የተገለጹበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ ወይም የከበደ መሆን አይኖርበትም፡፡

8. የጥያቄዎቹ መልሶች ተማሪው በደረጃው ሊኖረው ከሚገባው የቋንቋ ብቃት የሚልቅ የቋንቋ አጠቃቀም መጠየቅ የለባቸውም፡፡
9. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የተማሪውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉበት መንገድ እንጂ የተማሪውን ችሎታ የሚፈትኑ ዓይነት ሆነው መቅረብ አይኖርባቸውም፡፡
10. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበትን መንገድ ማፈላለግ አስፈላጊ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከተመረጡት ምንባቦች ጥያቄዎች በሚወጡበት ጊዜ ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ዋና ዋና ሀሳቦችን፣ መረጃዎችን፣ ነጥቦችን፣ ምሳሌዎችን ወዘተ. በማስታወሻ በመያዝ ለጥያቄ ማውጫ መጠቀም ይቻላል፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና በሚጻፍበት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ማስገባት እንዳለብን Hughes ( 1989፡130) እና Madsen (1983፡ 83-84) ይገልጻሉ፡፡

1. ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ የምንባቡን ሀሳብ ሳይረዱ ወይም ሳይገነዘቡ ወይም ምንባቡን ሳያነቡ የሚመልሱዋቸው መሆን የለባቸውም፡፡
2. የጥያቄዎቹ መልሶችም በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ወይም በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሊሆኑ ይገባል፡፡
3. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የምንጠቀማቸው ምዘናዎች ከተወሰነ ባህል ጋር የተሳሰሩ መሆን የለባቸውም፡፡ ባህሉን የምንፈትን ካልሆነ፡፡
4. እንዲሁም ጥያቄዎቹ ከምንባቡ እንዳለ ቃል በቃል ተወስደው የቀረቡ መሆን የለባቸውም፡፡ ነገር ግን በቀላልና ግልጽ ቋንቋ መጻፍ አለባቸው፡፡
5. አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የምናዘጋጀው ፈተና ከቋንቋ ክሂል ውጭ በሆነ እውቀት የሚመለስ መሆን አይኖርባቸውም፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የምናዘጋጃቸው ፈተናዎች ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሁሉንም የምንባቡን ክፍሎች የሚዳስሱ ከምንባቡ መጠን አኳያ በቂ ቁጥር ያላቸው ፣ በአይነት የተለያዩና ልዩ ልዩ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚረዱ፣ የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ሂደት የሚደግፉና የቋንቋ ችሎታ ደረጃቸውን ያገናዘቡ እንዲሆኑ Nuttal (2000፡

190) ይመክራሉ፡፡ እስካሁን ከቀረቡት ሀሳቦች የምንረዳው የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ሲዘጋጁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ነው፡፡

Nuttal (1982: 37) አንድ አንባቢ የአነበበውን ጽሁፍ ካልተረዳ ማንበቡ ዋጋ የለውም፡፡ ስለዚህ መረዳት መታወቅና መወሰን አለበት፡፡ ይህን ሁኔታ እንደ ዓላማ ለመውሰድ ምርጫ፣ የእውነት (ሐሰት) ጥያቄዎችን በመጠቀም መለካትና ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ግን የትኛው ውጤት እንደ ጥሩ መረዳት ይወሰድ? በአጠቃላይ አመለካከት ሲታይ 70% መረዳት ይበቃል፡፡ የትኛውስ የተሸለ አንባቢነው? 100% ውጤት አግኝቶ በደቂቃ 140 ቃላት ያነበበው ወይስ 70% ውጤት አግኝቶ በደቂቃ 200 ቃላት ያነበበው? የትኛው ውጤት አጥጋቢ ነው? ወይም የትኛው ጥሩ አንባቢ ነው? ወዘተ. ለሚሉት ጥያቄዎች ቁርጥ ያለ መልስ አላገኙም፡፡ ነገር ግን 70% አንብቦ የመረዳት ችሎታ በቂ ነው የሚል እይታ እንዳላቸው Nuttal ( 2000:58) ይገልጻሉ፡፡

በቂ የማንበብ ፍጥነትን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን የሚሰጡት አስተያየት አንድነት አይታይበትም፡፡ Anderson ( 1999:3) እንደገለጹት የማንበብ ፍጥነትን አስመልክቶ የሚወጡ መረጃዎች እርስ በርሳቸው የሚጋጩበት ሁኔታ አለ፡፡ አንዳንድ ፀሐፊዎች በብቃት አንብቦ ለመረዳት ከተፈለገ በደቂቃ 180 ቃላትን ማንበብ መቻል እንደ ዝቅተኛ የማንበብ ፍጥነት ሊወሰድ ይችላል ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በደቂቃ 200 ቃላትን ከመቶ በመቶ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ማንበብ እጅግ አነስተኛ ፍጥነት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም አንዳንዶቹ ምሁራን በደቂቃ 300 ቃላትን ማንበብ መቻል በቂ የማንበብ ፍጥነት ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም በቂ የማንበብ ፍጥነትን በሚመለከት ቁርጥ ያለ ብያኔ ለማግኘት ያስቸግራል፡፡

> ከዚህ በተጨማሪ Nuttal ( 2000:56) እንግሊዘኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምንም አይነት ልዩ ስልጠና ሳይወስዱ ከመቶ ሃያ እስከ መቶ ሀምሳ ቃላት በአንድ ደቂቃ ማንበብ እንደቻሉና በእነዚሁ በተመሳሳይ አካባቢዎች ያሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በደቂቃ 200 ቃላት ማንበብ እንደሚችሉ ተገምቷል ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ምንባቡ ከባድ በሚሆንበት ጊዜና የጽሑፉን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ መገንዘብ ወይም መረዳት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በደቂቃ 60 ቃላት ብቻ እንደሚያነቡ ታውቋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል የማንበብ ፍጥነት በሂደት የሚዳብር መሆኑ በስፋት ይነገራል፡፡ በርግጥ

የሚማሩት ቋንቋ አፍ- መፍቻ ቋንቋቸው ላልሆነ ተማሪዎች የማንበብ ፍጥነትን የማሻሻሉ ጉዳይ ቀላል ተግባር አይደለም፡፡ ሆኖም ግን ተማሪዎቹ የማንበብ ፍጥነትን ማሳደግ የሚቻል መሆኑንና የማንበብ ፍጥነትን ጠቃሚነት ወይም ሚና ከተገነዘቡ በሂደት የማንበብ ፍጥነታቸውን ማሻሻል ይችላሉ፡፡

ተማሪዎች በደቂቃ ምን ያህል ወይም ስንት ቃላት ማንበብ አለባቸው? የሚለውን ሀሳብ Anderson ( 1999:3) ሲገልጹ በዚህ ጉዳይ ላይ በምሁራን መካከል የሀሳብ ልዩነት መኖሩን ካመለከቱ በኋላ የሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች ሰባ ከመቶ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር በደቂቃ 200 ቃላት ማንበብ መቻል ምክንያታዊ በመሆኑ ይህ ደረጃ ወይም መጠን እንደ መስፈርት እንደሚያገለግል ይጠቁማል፡፡ አክለውም ተማሪዎች ቢያንስ በደቂቃ 200 ቃላትን ከ70% አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር መስራት እንዲችሉ ሊበረታቱ ይገባል በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ወደዚህ ደረጃ ለመድረስ ባለማቋረጥ ልምምድ ቢያደርጉ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ብቁ አንባቢ ለመሆን ይህ ሂደት ወሳኝነት ያለው ነው፡፡

በሌላ በኩል አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚዘጋጁ ምንባቦች ለአንባቢዎቹ የሚስማሙ እንዲሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሲባል የሚመረጠው ምንባብ የክብደት ደረጃው፣ ውስብስብነቱ፣ ባህላዊ ገፅታው፣ የቀረበበት ርዕስና መጠኑ የተማሪዎችን ደረጃ ያገናዘበ መሆን አለበት Heaton (1975:112)፡፡ እዚህ ላይ ግን ለተማሪዎቹ ቅርበት ያላቸውንና ተማሪዎቹ ከዚህ በፊት ያነበቡዋቸውን ፅሁፎች እንዳናቀርብ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲባል ግን ምንባቦቹን ተማሪዎቹ ከዚህ በፊት ማንበብ አለማንበባቸውን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ወቅት የፈተናዎቹ አስተማማኝነት(reliability) እናትክክለኛነት(validity) ታሳቢ መሆን ይኖርባቸዋል Heaton (1991:159):: ትክክለኛነት ፈተናው ለመፈተን የተፈለገውን ችሎታ ወይም ክሂል በትክክል መለካት መቻሉን የሚመለከት ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን አስተማማኝነት ደግሞ አንድ ፈተና ተደጋግሞ ቢሰጥ የሚያስገኘው ውጤት ምን ያህል እንደሚቀራረብ የሚያመለክት ነዉ (Hughes 1989:3)::

ለችሎታ መለኪያነት የሚዘጋጅ ፈተና በትክክል የተማሪዎችን ችሎታ ለመለካት የሚያስችል መሆኑ በባለሙያዎች ሊታይና አስተያየት ሊሰጥበት ይገባል፡፡ እንዲሁም አንድ ፈተና በስፋት ለተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት የሙከራ ፈተና (pilot test) በመስጠት ትክክለኛነት መለካት

አስፈላጊ ይሆናል Heaton (1991:163-164)፡፡ Madsen ( 1983:89) የበሳል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የምንጠቀመው ምንባብ ከ100 እስከ 300 ቃላት ያሉት ወይም ከ100 እስከ 200 ቃላት ያሉት ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡ እንዲሁም ይህ አሀዝ እጅግ ጠቅለል ባለ መልኩ የተገለጸ እንደሆነ የምንባቡ ርዝመት ወይም መጠን እንደሁኔታው ሊለያይ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ የምንጠቀመው ምንባብ መጠን አንድ ወጥ ላይሆን ይችላል፡፡

የአንብቦ መረዳት ፈተና ሲዘጋጅ የተፈታኞችን የንባብ ፍላጎት ለመጠበቅና እኩል እድል ለመስጠት ቢያንስ ሁለት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዙ ምንባቦች ተመርጠው ጥያቄዎቹ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ የምንባቦቹ የተገቢነት ደረጃ በፈተናው ውጤት ላይ ተፅዕኖ ስለሚኖረው በጥንቃቄ መምረጥ ተገቢ ይሆናል (Madsen 1983:89) ::

እንደ Madsen (1983:90) አከፋፈል እንደ ተፈታኞቹ የክፍል ደረጃ ሊለያይ የሚችል ሲሆን ለዝቅተኛ ወይም ለመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ከ100 እስከ 200 ቃላት፣ ለመካከለኛ ደረጃ ከ150 እስከ 300 ቃላት የያዙ ምንባቦች ሊመረጡ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ፡፡ Heaton (1991:112) ደግሞ ለዝቅተኛ ክፍሎች ከ50 እስከ 100 ቃላት፣ ለመካከለኛ ደረጃዎች ከ200 እስከ 300 ቃላት እና ለከፍተኛ ደረጃ ከ400 እስከ 600 ቃላት ያላቸው ምንባቦች ሊመረጡ እንደሚችሉ ያመለክታሉ፡፡ ለአንብቦ መረዳት ፈተና የሚያስፈልገው ጊዜ በሙከራ ፈተናው ላይ ተመስርቶ መወሰን እንዳለብን Madsen (1983:89) ይገልጻሉ፡፡

ቀደም ሲል አንብቦ የመረዳት ችሎታን በመለካት ሂደት የተለያዩ አይነት ፈተናዎችን መጠቀም ተገቢ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ምክንያቱም Weier ( 1990፡ 42) እና ሌሎች ምሁራን እንደገለጹት እያንዳንዱ የፈተና አይነት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን አለው፡፡ የተለያዩ ፈተናዎችን መጠቀም የሚመከረው ለዚህ ነው፡፡ ስለሆነም ለምሳሌ ሁለት አይነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን የተጠቀምን እንደሆነ የሁለቱን ፈተናዎች አማካይ ውጤት በመውሰድ የተማሪዎች ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መግለጽ እንችላለን፡፡ ለዚህ ጥናትም የምርጫ ጥያቄዎችና የእውነት/ ሐሰት ጥያቄዎች ከተዘውታሪነታቸውና ከውጤታማነታቸው አንጻር ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ አንብቦ መረዳትን ለማረጋገጥ የሚዘጋጁ ፈተናዎች በጥንቃቄ መዘጋጀት እንዳለባቸውና በባለሙያ አስተያየት ሊሰጥባቸው እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### 2.4. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን መስፈርቶች አስቀምጠዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ Hughes (1989:119) እንደሚገልጹት በመሰረቱ አንድ ጽሁፍ የያዘውን ሀሳብ ወይም መልዕክት ተፈታኞች ሙሉ በሙሉ ተረድተውታል ለማለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በሙሉ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገርግን የሰው አዕምሮ በጽሁፍ የቀረቡ ሀሳቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት የሚገነዘብ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ተፈታኞች ከ80 በመቶ በላይ ውጤት ካስመዘገቡ የቀረበውን ጽሁፍ ተረድተውታል ማለት እንደሚቻል ያስረዳሉ ፡፡

ምክንያቱም ለማንበብ ፍጥነቱም ሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የተለያዩ አንባቢዎች በተለያየ ፍጥነትና የመረዳት ችሎታ ደረጃ የሚያነቡ ስለሆነና እሳቤዎቹም በአንጻራዊነት የሚገልጹ ስለሆነ የደረጃ መስፈርቱ ከፍ ሲል በተገለጸው መሰረት ቢቀመጥ የተሻለ እንደሚሆን ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡

በሌላ በኩል Madsen (1983:91) እና ሌሎች ተማሪዎች ከበቂ ፍጥነት ጋር በተሰጣቸው የችሎታ መለኪያ ፈተና ያመጡት ውጤት ከ40% በታች ከሆነ በጣም ዝቅተኛ፣ ከ50-41% ዝቅተኛ፣ ከ69-51% መካከለኛ፣ ከ70-80% በቂ፣ 81% እና ከዚያ በላይ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው በማለት ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ፍጥነት እንደ አንባቢዎች የሚለያይ ስለሆነ ነው፡፡

Narayanswamy (1975፡144-147) ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤትን ሲገልጹ ከ10 ከታረመ ፈተና ከ9-10 ውጤት ያስመዘገቡ ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ7-8 ያስመዘገቡ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ5-6 ያስመገዘቡ ዝቅተኛ እና ከ5 በታች ያስመዘገቡ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተብለው እንደሚፈረጁ ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ ስንመለከት በተለይ አማካይ ችሎታ ያላቸውን ተፈታኞች በተመለከተ የመቀራረብ ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ይችላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ከ10 ከታረመ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ከ9-10 ያገኙ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው፣ በፈተና ውጤቱ ከ7-8 ያገኙ በቂ ችሎታ ያላቸው ሲሆኑ በአንጻሩ ከ5

እስከ 6 ውጤት ያገኙ ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸው እና ከ5 በታች ውጤት ያገኙ በጣም ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ይህ የደረጃ መስፈርት የተፈታኞችን የችሎታ ደረጃ ለመመዘን የተሻለ እንደሚሆን ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

### 2.5. የንባብ ፍጥነት ምንነት

እንደ Nuttal (1982:36) ገለጻ የንባብ ፍጥነት ማለት አንድ አንባቢ ከተጻፈ ጽሁፍ ላይ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ ያነባል ማለት ሲሆን የንባብ ፍጥነት የሚለካው በደቂቃ ውስጥ በምናነበው የቃላት ብዛት ይሆናል፡፡ የንባብ ፍጥነት ሲሰላ የሚከተለውን ቀመር መሰረት ያደርጋል፡፡

**x/y x 6= z**

X= በጽሁፍ ውስጥ ያሉት የቃላት ብዛት

Y= በፅሁፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት ለማንበብ የወሰደው ሰአት በየአስር ሴኮንድ ልዩነት

6 = በደቂቃ ውስጥ የሚኖር  የ10 ሴኮንድ ልዩነት

Z= በደቂቃ ውስጥ የሚነበበውን የቃላት ብዛት የሚያመለክት ነው፡፡

ይህን ስሌት መሰረት አድርጎ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ እንዳነበቡ ማወቅ ይቻላል፡፡

ለዚህም የሚረዳ የንባብ ፍጥነት መቆጣጠሪያ ቻርት ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ቻርት ከ1 እስከ 6 ቁጥሮችን የያዘ ሲሆን 1 ደቂቃን ያመለክታል፡፡ ቁጥሮቹ በየ10 ሴኮንድ ያለውን ክፍተት ያመለክታሉ፡፡ ይህም ማለት በ10 ሴኮንድ የጨረሰ አንድ ቁጥር በሃያ ሴኮንድ የጨረሰ ሁለት ቁጥር እያለ የሚቀጥል ነው፡፡ ይህ ቻርት አዝጋሚ አንባቢዎች ይፈጅባቸዋል ተብሎ እስከሚገመተው የጊዜ ገደብ ከተዘጋጀ በኋላ የእያንዳንዱ ተማሪ የንባብ ፍጥነት በቻርቱ መሠረት ይመዘገባል፡፡ ከዚያም ቀደም ሲል በተገለጸው መሠረት ምን ያህል ቃላት በደቂቃ እንዳነበቡ ይሠላል፡፡

Anderson (1999:104) " የንባብ ፍጥነት ክህሎትን ማዳበር ለተማሪዎች እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ በክፍል ውስጥ ግን የተተወ ወይም የተረሳ ክሂል ነው፡፡" ብሏል ይህንን ሀሳብ Grabe ና Stoler (2002:19) በሚከተለው መንገድ ገልጸውታል "አንድ የሚነበብ የቤት ስራ ለተማሪዎች

እንሰጣቸዋለን፡፡ ይህንን ስራ ከሰጠናቸው በኂላ ስራውን ለማንበብ ምን ያህል ጊዜ እንደፈጀባቸውና በምን መንገድ እንደተረዱት አንጠይቃቸውም፡፡ አንዱ ተማሪ በ30 ደቂቃ አንብቦ ሰርቶት ይሆናል፤ ሌላው ደግሞ አንድ ሌሊት ወስዶበት ይሆናል፤ ይህም ሆኖ ምንባቡን ላይረዳ ይችላል፡፡ ይህንን ከግንዛቤ አስገብተን ማለትም በምን ያህል ጊዜ (ፍጥነት) እንዳነበቡትና እንደተረዱት በአግባቡ አውቀን ተማሪዎቻችንን አናርማቸውም ወይም በማለማመድ አናስተካክላቸውም፡፡ በመሆኑም በንባብ ፍጥነት ደካማ የሆኑ ተማሪዎች እንዲሁ ባሉበት ሁኔታ ይቀራሉ" ብለዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነትና የመረዳት አቅማቸውን ተገንዝቦ እገዛ ማድረጉ ትኩረት ያልተሰጠው እንደሆነ ነው፡፡

ሌላው እንደምናነበው ነገር ወይም ይዘት የምናነበው የቃል ቁጥር በደቂቃ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡ ይህንን አስመልክተው Nuttal (1982 :47) የሚከተለውን ይገልፃሉ፡፡ የንባብ ፍጥነታችን እንደምናነበው ጉዳይ ይለያያል፡፡ ይኸውም ከአሰሳ ንባብ እስከ ጥልቅ ንባብ ድረስ ያሉ የንባብ ቴክኒኮችን የሚፈልግ ሊሆን ይችላል፡፡ የመዝናኛ ንባብና የጥናት ንባብ ፍጥነት ይለያያል፡፡ ይህን ማወቅ ለፍጥነት ንባብ አጠቃቀም አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የንባብ ፍጥነት ክህሎት ማዳበር ብቻ መረዳትን ያመጣል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በንባብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቴክኒኮች (ይዘቶች) በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በአንብቦ መረዳት ላይ ና በፍጥነት ንባብ ላይ የራሳቸው ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

ይሁንእንጂ ለአንብቦመረዳት ያለው አስተዋጽኦ ግን ቸል የሚባል ጉዳይ አይሆንም፡፡ የተለያዩ የቋንቋ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ይበረታታሉ፤ በተገቢው የንባብ ሂደት ውስጥ እንዲገቡና እንዲያነቡ ይሰለጥናሉ በማለት Anderson (1999:112) ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች ከሚያነቡበት አላማና ከሚያነቡት የጽሁፍ ዓይነት አንጻር የንባብ ስልትና ፍጥነታቸውን በመለዋወጥ የማንበብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት አስፈላጊነው፡፡

## 2.6. የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ

የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ እንዳለው ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ Nuttal (1982:33) ጥሩ አንባቢ ቃል በቃል አያነብም፣ ከደካማ አንባቢ በተሻለ ፈጣን የአይን እንቅስቃሴ ሲኖረው በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቃላትን

የመቃኘት ችሎታ አለው። እንዲሁም የጥሩ አንባቢ ባህሪ በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቃላት በመቃኘት ቃል በቃል ሳይሆን በአፍታ እይታ ማንበብ መቻል ነው። ፈጣን አንባቢዎች በአንድ በተፃፈ ነገር ላይ ያለውን ቃል እየቆጠሩ ሳይሆን አያይዘውና አከታትለው ስለሚያነቡ የሀሳብ መቆራረጥ ወይም መበጣጠስ ችግር አያጋጥማቸውም። ይህም የተሟላና ትርጉም ያለው ሃሳብ ለመያዝ ያግዛቸዋል። በመሆኑም የመረዳት አቅማቸውም ከፍተኛ ነው። በሌላ መልኩ አዝጋሚ አንባቢዎች የመረዳት አቅማቸው ደካማ ነው ማለታችን ነው። ምክንያቱም ሃሳቡን ቆራርጠው ስለሚያነቡ የአርፍተነገሩንም ሆነ የአንቀጹን ሃሳብ ተያያዥ በሆነ መልኩ አያገኙትም። በዚህም መጨረሻ ላይ ሲደርሱ የመጀመሪያው ምን እንደሆነ መረዳት አይችሉም። አንባቢው አንብቦ ከጨረሰ በኋላ የሚያስበው ስላነበባቸው ተናጠል ቃላት እንጂ ስለአጠቃላይ ፅሁፉ አይደለም። በዚህም የመረዳት ችግር ያጋጥመዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ መረዳት ጋር የተሳሰረ መሆኑን ነው። Anderson (1999:2) ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩት በቂ የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያነበቡትን ጽሁፍ ወይንም ምንባብ በብቃት መረዳትና ማስታወስ ብቻ ሳይሆን በተቻለ መጠን በጥሩ ፍጥነት አንብቦ መረዳትንም የሚያጠቃልል መሆኑንና አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነትም ጎን ለጎን ሊዳብሩ እንደሚገባ ገልፀው በማከልም ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸውን አሳድገው ጥሩ አንባቢ ሊሆኑ የሚችሉት የንባብ ፍጥነታቸውን ብቻ ሳይሆን አንብበው የመረዳት ችሎታቸው አድጎ ጥሩ ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው በማለት ይገልፃሉ።

Perfetti (1985 : 12) ደግሞ በሚከተለው መንገድ ገልጸውታል፤ “ የንባብ ችሎታ ብያኔ የሚመነጨው ከንባብ ፍጥነትና ከአንብቦ መረዳት ግንዛቤ ውስጥ ነው። ስለዚህ አንድ ጥሩ የንባብ ችሎታ ያለው ሰው በአማካይ ከሚታወቀው የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ደረጃ በላይ አንብቦ መረዳትና በፍጥነት ማንበብ ይጠበቅበታል። ይህም የንባብ ችሎታ መለኪያ ዕድሜንና የትምህርት ደረጃን መሰረት ያደረገ ይሆናል” በማለት ያስረዳሉ። ከዚህ የምንረዳው የንባብ ችሎታ ማለት ከንባብ ፍጥነትና አንብቦ ከመረዳት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። ይህንኑ ሀሳብ Perfetti (1985 : 10) ሲያጠቃልሉ“ መሰረታዊ የሆኑት የማንበብ ችሎታ መለኪያዎች የንባብ ፍጥነትና ጥሩ የመረዳት አቅም ናቸው” ብለዋል። ስለዚህ የንባብ ፍጥነት ደረጃችንና አንብቦ የመረዳት አቅማችንን በየጊዜው ማሻሻል ይገባል። ይህንን አስመልክተው Bell (2001 : 101) ባጠኑት ጥናት እንዳመለከቱት በፍጥነት የሚያነቡ ሰዎች ወሳኝ በሆነ መልኩ ከፍተኛ የሆነ የመረዳት ችሎታ አላቸው በማለት ገልጸው ይህንንም እንደሚከተለው አብራርተዋል።

ከፍተኛ የንባብ ችሎታ ያላቸው አንባቢዎች 1000 ቃላት በደቂቃ ሲያነቡ፤የመረዳት ችሎታቸው ደግሞ 85% እንደሆነ በመጥቀስ እነዚህም ከአጠቃላይ አንባቢዎች 1% የሚሆኑ መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡ አያይዘውም አብዛኛዎቹ አንባቢዎች 200 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሲሆኑ የመረዳት ችሎታቸው 60% እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት መካከለኛ አንባቢዎች ከፈጣን አንባቢዎች አምስት ጊዜ እጥፍ ያዘግማሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከንባብ ንዑሳን ክሂሎች ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ነው፡፡ የፍጥነት ንባብም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ አንብቦ መረዳትና የንባብ ፍጥነት በአንድነት መዳበር ያለባቸው ክሂሎች እንደሆኑ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ በፍጥነት ማንበብ ነገሮችን በቀለጠፈ መልኩ ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ዘገምተኛ አንባቢዎች አንድን ጽሁፍ አንብበው የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም አንብቦ መረዳት ከፍጥነት ንባብ ክሂል ጋር ዝምድና እንዳለውና የአንዱ መኖር ለአንዱ ህልውና ወሳኝነት እንዳለው ይገልጻሉ (Nutall 1982፡33) ፡፡

በሌላ በኩል Anderson (1999) ዝቅተኛ የንባብ ልምድ ያላቸው ማለትም ፊደል በመቁጠር የሚያነቡ በደቂቃ 1- 100 ቃላት ሲያነቡ የመረዳት አቅማቸው ከግማሽ በታች ነው፡፡ ዕድሜያቸው ከ6–12 የሆኑ ተማሪዎች ከ100–200 ቃላት በደቂቃ ማንበብና 50% የመረዳት አቅም እንዲኖራቸው ይፈለጋል ፡፡በአብዛኛው አንባቢ ደግሞ ከ200–250 ቃላት በደቂቃ ማንበብና ከ50% በላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ይጠበቅበታል፡፡ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ከ250–350 ቃላት በደቂቃ ማንበብ ሲኖርባቸው የመረዳት አቅማቸውም ከግማሽ በላይ መሆን አለበት፡፡ የተሻለ የማንበብ ደረጃ ላይ የሚገኙና ጥሩ የመረዳት አቅምና ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ከ350–500 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሲሆን 75% አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው፡፡ በጣም ውጤታማ የሆኑ አንባቢዎች ከ800–1000 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሲሆን ከ75% በላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው 1000 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ሰዎች እጅግ በጣም ጥሩ አንባቢዎችና የመረዳት አቅማቸውም ከፍተኛ እንደሆነ ሲሆን ከ1–100 ቃላት በደቂቃ የሚያነቡ ደግሞ ዘገተኛ አንባቢዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ የመረዳት አቅማቸው ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.7. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ ጥናቷን ከመጀሯ በፊት ከርዕሷ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች ለመቃኘት ሞክራለች፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ላይ ሲሆን ከዳሰሰቻቸው ጥናቶች መካከል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን የሚከተሉትን ጥናቶች ቃኝታለች፡፡

መኮንን (2000) በአዊኛ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ግምገማ፡፡ የመኮንን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ መገምገሙ ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ትኩረቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ተዛምዶ የሚፈትሽ መሆኑ ያለያያቸዋል፡፡ ሌላው ጥናቱ የተደረገበት ቦታና ዘመን ሌላው የሚያለያያቸው ጉዳይ ነው፡፡

ተሾመ (1997) በካምባታ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ፍጥነታቸው በሚል ርዕስ ያጠኑት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ቢኖረውም ከክፍል ደረጃ ከቦታና ከዘመን ልዩነት በተጨማሪ በመረጃ መሰብሰቢያና በመረጃ ምንጮች ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ኢ-አፍፊት በሆኑ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ ከተሾመ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

አያሌው (2001) በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንብቦ የመረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ፡- በወልድያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ ጥናት በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ቋንቋው በአፍ መፍቻነትና በትምህርት መስጫነት በስፋት በሚያገለግል ክልል ውስጥ የተካሄደ በመሆኑና በመሰናዶ ተማሪዎች ላይ የተደረገ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት ያለው ሆኖ እናገኛለን፡፡ ምክንያቱም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በ9ኛ ክፍል ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ላይ በመሆኑ ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን ነገርግን አሁንም አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ዝቅተኛ እንደሆነና አሁንም ትልቅ ሥራ እንደሚጠበቅ መረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቶቹ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም የሁሉም ጥናት ዓላማ የተለያየ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ሲሆን ትኩረት የሚያደርገው በሠገን ሁለተኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ እንደሆነ በክፍል አንድ ተገልጿል፡፡ ለዚህም ወካይ የሆኑ ተማሪዎች በናሙናነት ተወስደው መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በመጠናዊ ገላጭ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በዋናነት መጠናዊ የምርምር ስልትን የሚከተል ሲሆን በደጋፊነት ደግሞ አይነታዊ የምርምር ዘዴ የሆነውን ገላጭ የምርምር ስልት የሚከተል ሲሆን ከችሎታ መለኪያ ፈተናውና ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የሚገኙ መረጃዎች በአሀዝና በገለጻ የሚያቀርብ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በአንብቦ የመረዳት ችሎታ እና በንባብ ፍጥነት መካከል ያለው ዝምድና በSPSS የኮምፒውተር ፕሮግራም በመጠቀም ተሰልቶ ውጤቱ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 3.2. ተጠኚዎችና የናሙና አወሳሰድ

#### 3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ 14 ዞኖች መካከልየሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡ ምክንያቱም ጥናቱን ለማካሄድ በቅርበት የሚገኝ ዞን በመሆኑ ነው፡፡ የሠገን  አካባቢ ሕዝቦች ዞን ከሚገኙ 25 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የሰገን 2ኛ ደረጃና መሰናዶትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ቤቱ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ኢአፈፈት ተማሪዎችን የያዘ በመሆኑና መምህርቷም የምታስተምርበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ወጪ፣ ጉልበትና ጊዜን ይቆጥባል ተብሎ ታስቦ ነው፡፡

### 3.2.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ዘጠነኛ ክፍል ለጥናቱ ተስማሚ በመሆኑ በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ ምክንያቱም ይህ የክፍል ደረጃ የሁለተኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል መጀመሪያ በመሆኑና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን የንባብ ችሎታና ፍጥነት ለመለካት አመቺ በመሆኑና ተማሪዎች ለደረጃው የሚፈለገውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ይዘው መምጣታቸውን ለመፈተሽ ነው፡፡

### 3.2.3. የተማሪዎች አመራረጥ

በሠገን 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በ2010 ዓ.ም. በ9ኛ ክፍል ከሚማሩ 409 ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ኢአፍፊት የሆኑ100 ተማሪዎች በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ ሲሆን 25 ተማሪዎች አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ፣ 25 ተማሪዎች አፋቸውን በኮንስኛ የፈቱ፣ 25 ተማሪዎች አፋቸውን በኮረቴ የፈቱና 25 ተማሪዎች አፋቸውን በደራሽኛ የፈቱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ያተኮረው በኢአፍፊት ተማሪዎች ላይ ስለሆነ አፈፊቶችን ከኢአፍፊት ለመለየት ሲባል ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያነት የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያዎች ሁለት ሲሆኑ እነሱም ፈተና እና ለመምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.3.1.ፈተና

ለጥናቱ የተመረጠው ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ነው፡፡ ለዚህም ሁለት አይነት ፈተናዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህም የንባብ ፍጥነትን እና የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚለኩ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ፈተናዎቹም በትምህርት ቤቱ በሚገኙ ሦስት የአማርኛ መምህራን በአርባምንጭ መምህራን ኮሌጅ በሚያስተምር አንድ የ2ኛ ዲግሪ መምህር እንዲሁም በአማካሪዬ አስተያየት ተሰጥቶባቸው የመጨረሻ ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡

ፈተናዎቹ የተማሪዎቹን የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዲመዝኑ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ምንባብ ልብወለድ ጽሁፍ ሲሆን 340 ቃላት ሲኖረው

ሁለተኛው ምንባብ ደግሞ ኢ-ልብወለድ ጽሁፍ ሆኖ 394 ቃላትን የያዘ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ (አባሪ “1” እና “2”ን ይመልከቱ )፡፡

በእነዚህ ምንባቦች የንባብ ፍጥነታቸው የተለካ ሲሆን አንብቦ መረዳትን ለመለካት አስር አስር ጥያቄዎች በማውጣት አንብቦ የመረዳት ፈተና ተዘጋጅቷል፡፡ የንባብ ፍጥነትን ለመለካት የNuttall (1982፡36) የፍጥነት መለኪያ ስሌት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

ፈተናው ደረጃውን የጠበቀና ትክክለኛነት እንዲኖረው በሌላ በአቅራቢያ በሚገኝ ለጥናቱ ባልተመረጠ በበረቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሙከራ ፈተናው ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ፈተናዎቹ የሚፈለገውን መረጃ የሚያስገኙ እና ትክክለኛነት ያላቸው መሆናቸው ተረጋግጦ ከስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በመጨረሻም ከተማሪዎቹ ጋር በመነጋገር ከትምህርት ቀን ውጪ በሁለት ቅዳሜ ቀናት ምንባቡን እንዲያነቡ በማድረግ የንባብ ፍጥነታቸው ተለክቷል፡፡ በተመሳሳይ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኂላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ለዚህም አጥኝዋን ጨምሮ አራት መምህራን በመረጃ አሰባሰብ ስራ ላይ ተሳትፈዋል፡፡

### 3.3.2.ቃለ መጠይቅ

በአጋዥነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የመምህራን ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ በአንድ ጉዳይ ዙሪያ ጥልቅ የሆነ፣ ስፋት ያለውና የተብራራ ምላሽ ለማግኘት ከማስቻሉም በላይ የተሰጠውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥና በመላሹ በጽሑፍ ያልተገለጹ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና አማካይነት የተገኘውን መረጃ ለማዳበር ያመች ዘንድ ከጥናቱ ተተኳሪዎች ውጭ 9ኛ ክፍል አማርኛን ለሚያስተምሩ ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመጠኑ የተደራጀ ቃለ መጠይቅ ቀርቦ መረጃው ተሰብስቦና ወደ ጽሑፍ ተገልብጦ ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡

በቃለ መጠይቁ የመምህራኑ አጠቃላይ ዳራ፣ በክፍል ውስጥ ንባብ የሚያቀርቡበት ዘዴና ስለተማሪዎቻቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ያላቸውን አስተያየት እንዲሁም ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት የሚገጥማቸውን ችግርና የመፍትሔ ሀሳቦችን ያመላከቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ጥያቄዎቹም በአጥኚዋ አስቀድመው ከተዘጋጁ በኂላ በአማርኛ ቋንቋ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ታይቶ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

በተጨማሪም በጥናቱ አማካሪ መምህር ተገምግሞ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ (አባሪ "5"ን ይመልከቱ) ፡፡

## 3.4. የመረጃ አሰባሰብ

ተጠኝዎች ከተመረጡ በኋላ በአጥኝዋና በረዳት መምህራን አማካኝነት የጥናቱ ዓላማና እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ ፈተናው የንባብ ፍጥነታቸውንና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካትና ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ ብሎም መፍትሔ ለመፈለግ የተዘጋጀ በመሆኑ በራሳቸው እንዲሰሩ ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡

ፈተናው በሚሰጥበት ወቅት አጥኝዋ ከረዳት መምህራን ጋር በመሆን እያንዳንዱ ተማሪ ድምጽ ሳያሰማ እንዲያነብ ተደርጓል፡፡ አንብቦ የጨረሰበትን ሰአት የተማሪዎችን ዝርዝር በያዘው ቻርት ላይ በምን ያህል ሴኮንድ እንዳነበቡ ተመዝግቦ ተይዟል፡፡

ከዚያም የፍጥነት መለኪያ ምንባብ ፈተናው ተሰብስቧል፡፡ በመቀጠል የአንብቦ መረዳት ጥያቄ የያዘውን የጥያቄ ወረቀት በመስጠት ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም ምንባቡና የአንብቦ መረዳት የተፈተና ጥያቄው አንድ ላይ የሚሰጥ ከሆነ ወደ ኋላ ሄደው ምንባቡን እያዩ ጥያቄዎቹን እንዳይሰሩ ታስቦ ነው፡፡ በመጨረሻም አጥኝዋና ረዳት መምህራን የተማሪዎችን ዝርዝር በመያዝ እያንዳንዱ ተማሪ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ እንዳነበበና ምን ያህል ጥያቄ እንደመለሰ ታርሞ ተመዝግቦ ተይዟል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሰገን 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚገኙ ኢ-አፍ ፊት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ስለሆነም በአንብቦ መረዳት ችሎታና በንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ተዛምዶ በ (person product moment correlation) የስሌት ቀመር ተፈትሿል፡፡ የተገኘውም ውጤት በመጠናዊ ገላጭ የምርምር ስልትና እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ስታትስቲካዊ ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የንባብ ፍጥነት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ዝምድና ተፈትሾ ውጤቱ ተተንትኗል፡፡ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በይዘት ተከፋፍለው በመቶኛ እየተሰሉ ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል በመረጃ መሰብሰቢያው ማለትም በፈተናው አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች የተሰሩበትን የስሌት ቀመር መሰረት በማድረግ ስታትስቲካዊ ገላጭ ትንተና ይሰጥባቸዋል፡፡

### 4.1. የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች

አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነትን ለመለካት የተሰጡት ሁለት ፈተናዎች በውስጣቸው የእውነት /ሐሰት፣የምርጫ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡ ፈተናዎቹ በአጥኝዋና በረዳት መምህራን በጋራ ከታረሙ በኋላ ውጤቱ ተይዟል፡፡ በዚህም እያንዳንዱ ተማሪ በሁለቱ ፈተናዎች ያገኘው ውጤትና የሁለቱ ፈተናዎች አማካይ ውጤት እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተመዘገበው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ( አባሪ "4" ን ይመልከቱ)

በአባሪ 4 ያለው ሰንጠረዥ እንደሚያሳየን በአንብቦ የመረዳት ፈተና አንድ ከፍተኛው ውጤት 10 ከ10 ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 2 ከአስር ነው፡፡ የተጠኝ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ፈተና አንድ አማካይ ውጤት 6.06 ነው፡፡ ይህ የሚያሳየን በፈተና አንድ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ በአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ መደበኛ ልይይት 2.334718 ነው፡፡

በአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት የተመዘገበው ውጤት ደግሞ ከፍተኛው 10 ከ10 ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 1 ከአስር ነው፡፡ የፈተና ሁለት አማካይ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት 6.21 ሲሆን መደበኛ ልይይት 2.114381 ነው፡፡ ይህም ከፈተና አንድ በተመሳሳይ አብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው እንደሆነ ነው፡፡ የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድና ሁለት አማካይ ውጤት 6.135 ሲሆን መደበኛ ልይይት 1.708742 ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው  በአንብቦ መረዳት ላይ ሰፊ ችግር መኖሩን ነው፡፡ የእያንዳንዱ ፈተና ዝርዝር ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.1.1. የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና አንድ አንጻር

ሠንጠረዥ 1፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አንድ ውጤት

| ውጤት ከ10% | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 10 | 7 | 7 |
| 9 | 11 | 11 |
| 8 | 15 | 15 |
| 7 | 12 | 12 |
| 6 | 12 | 12 |
| 5 | 10 | 10 |
| 4 | 17 | 17 |
| 3 | 11 | 11 |
| 2 | 5 | 5 |
| 1 | 0 | 0 |
| 0 | 0 | 0 |
| ድምር | 100 | 100 |

ከሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ውጤት ከ10 ከተፈተኑት ፈተና ከፍተኛው ውጤት 10 ከአስር ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 2 ከአስር ነው፡፡ ከአጠቃላይ ቁጥሩ ውስጥ 55 ከመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች 6 እና ከዚያ በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ 45 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ 7 እና ከዚያ በላይ ውጤት አምጥተዋል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ከግማሽ በላይ የሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በፍጥነት የሚያነቡ ሰዎች ወሳኝ በሆነ መልኩ ፈጣን የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲኖራቸው ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ዝቅተኛ የመረዳት ችሎታ አላቸው በሚል በክለሳ ድርሳን በቁጥር 2.1.6 ከተገለፀው ሀሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡

### 4.1.2. የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፈተና ሁለት አንጻር

ሠንጠረዥ 2፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት ውጤት

| ውጤት ከ10% | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 10 | 5 | 5 |
| 9 | 10 | 10 |
| 8 | 13 | 13 |
| 7 | 16 | 16 |
| 6 | 19 | 19 |
| 5 | 9 | 9 |
| 4 | 16 | 16 |
| 3 | 9 | 9 |
| 2 | 2 | 2 |
| 1 | 1 | 1 |
| 0 | 0 | 0 |
| ድምር | 100 | 100 |

የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ሁለት እንደሚያሳየው የአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ከወሰዱ 100 ተጠኝ ተማሪዎች መካከል ከ10 ከተፈተኑት ፈተና ከፍተኛው ውጤት 10 ከአስር ሲሆን ዝቅተኛው ውጤት 1 ከአስር ነው፡፡ ከአጠቃላይ ቁጥሩ ውስጥ 56 ከመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች 6 እና ከዚያ በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ 44 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ 7 እና ከዚያ በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ እዚህ ላይ ከፍተኛ ውጤት 10 ከአስር ሲሆን የተመዘገበው በአምስት ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡ ይህ ከፈተና አንድ አንጻር ሲታይ ዝቅ ብሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ዝቅተኛ ውጤት የተመዘገበው 1 ከአስር ሲሆን የተመዘገበውም በአንድ ተማሪ ብቻ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው አብዛኛው ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችግር ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ሁለቱን የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ስንመለከት በፈተና አንድ 55 ከመቶ 6 እና ከዚያ በታች ሲያገኙ በፈተና ሁለት ደግሞ 56 ከመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች 6 እና ከዚያ በታች ውጤት አስመዝግበዋል። ይህ የሚያሳየን ውጤታቸው ብዙም ያልተራራቀና ተቀራራቢ ከመሆኑ ባሻገር አንብቦ መረዳት ላይ ከፍተኛ ችግር መኖሩን ነው።

### 4.1.3. የተጠኚ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ

በክለሣ ድርሳን 2.1.4 Narayanswamy (1995:144-147) የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤትን ሲገልጹ ከ10 ከታረመ ፈተና ከ9-10 ውጤት ያስመዘገቡ ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ7-8 ውጤት ያስመዘገቡ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው፣ ከ5-6 ውጤት ያስመዘገቡ ዝቅተኛ እና ከ5 በታች ውጤት ያስመዘገቡ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተብለው እንደሚፈረጁ ይገልጻሉ።

የዚህ ጥናት አቅራቢም ይህንን የሂሳብ ቀመር በመጠቀም በሚከተለው መልኩ ካስመዘገቡት ውጤት አንጻር መድባለች።

ሠንጠረዥ 3፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ የሚያሳይ

| ከ10% ያስመዘገቡት ውጤት | የፈተናው አይነት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፈተና አንድ | | ፈተና ሁለት | | አማካይ | |
| | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| ከ9-10 ያስመዘገቡ | 18 | 18 | 15 | 15 | 16.5 | 16.5 |
| ከ7-8 ያስመዘገቡ | 27 | 27 | 29 | 29 | 28 | 28 |
| ከ5-6 ያስመዘገቡ | 22 | 22 | 28 | 28 | 25 | 25 |
| ከ5 በታች ያስመዘገቡ | 33 | 33 | 28 | 28 | 30.5 | 30.5 |
| ድምር | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ከ10% ከተፈተኑት ሁለት ፈተናዎች በአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ከፍተኛ ቁጥር የያዙት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸው

ሲሆኑ ከ5 እስከ 6 እና ከ5 በታች ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው፡፡ ከ7 እስከ 8 እና ከ9 እስከ 10 ያስመዘገቡት ደግሞ መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው፡፡ በፈተና አንድ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ዝግተኛ አንባቢዎች ማለትም ከ5 እስከ 6 እና ከ5 በታች ውጤት ያስመዘገቡት 55% ሲሆኑ በፈተና ሁለት ደግሞ 56% ናቸው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በፈተና አንድ ከ7-8 ውጤት ያስመዘገቡ በቂ ደረጃ ላይ ያሉ አንባቢዎች በፈተና አንድ 27% ሲሆኑ በፈተና ሁለት ደግሞ 29% ናቸው፡፡ ፈጣን አንባቢዎች ማለትም ከ9 እስከ 10 ውጤት ያስመዘገቡ አንባቢዎች በፈተና አንድ 18% ሲሆኑ በፈተና ሁለት ደግሞ 15% ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ፈጣን አንባቢዎች ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተብሎ በተመደበው ከ9-10 ያለውን ውጤት ያስመዘገቡት 16.5% ሲሆኑ 28% አንባቢዎች ደግሞ በቂ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ተብሎ በተመደበው ከ7-8 ያለውን ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ 55.5% ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ከ5 እስከ 6 እና ከ5 በታች የሆነ ውጤት አስመዝግበው ይታያል፡፡ በመሆኑም በተገኘው ውጤት መሰረት ፈጣን አንባቢዎች በከፍተኛ አንብቦ መረዳት ደረጃና በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን ዝግተኛ አንባቢዎች ግን ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ምክንያቱም ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው አንባቢዎችን የሚያመላክት ነው ተብሎ በተፈረጀው እርከን ላይ ተመዝግበው የሚታዩት ዝግተኛ አንባቢዎች ናቸው፡፡ የፈጣን አንባቢዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ሆኖ ቢስተዋልም ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች በተሻለ ሁኔታ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.2. የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና ፈተና ሁለት ዝርዝር መረጃ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማዎች ከሆኑት ውስጥ አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነት ማጥናት ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ የታቀፉት የሠገን 2ኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢአፍ ፈት የሆኑ 100 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ ወይም ምንባብ ሲያነቡ በደቂቃ ምን ያህል ቃላት እንደሚያነቡ ለማወቅ ተሞክሯል፡፡ ለዚህም የተሰጡት የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ( አባሪ “3” ን ይመልከቱ)፡፡

### 4.2.1. የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ

ከአባሪ “3” ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በፈተና አንድ ዝቅተኛው ሰአት ወይም ፈጣን አንባቢ ምንባቡን አንብቦ ለመጨረስ የፈጀበት ሰአት 180 ሴኮንድ ሲሆን ከፍተኛው ሰአት ወይም ዝግተኛ አንባቢዎች ምንባቡን አንብቦ ለመጨረስ የፈጀባቸው 510 ሴኮንድ ነው። አማካዩ ደግሞ 300 ሴኮንድ መሆኑን እንረዳለን። መደበኛ ልይይት 71.5202874 ነው። በፈተና አንድ የቀረበው ምንባብ 340 ቃላትን የያዘ ነው። ምንባቡን አንብበው ለመጨረስ የወሰደባቸው ጊዜ እንዲመዘገብ ተደርጓል። ከዚያም ምንባቡ የያዛቸው የቃላት ብዛት ምንባቡን አንብበው ለመጨረስ በፈጀው ሴኮንድ በማካፈል የተገኘውን ውጤት በ6 በማባዛት የተማሪዎቹ የማንበብ ፍጥነት በደቂቃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 4፡ የተጠኝዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና አንድ

| የተጠኝዎች የማንበብ ፍጥነት በደቂቃ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 113 | 10 | 10 |
| 97 | 7 | 7 |
| 85 | 6 | 6 |
| 78 | 14 | 14 |
| 68 | 20 | 20 |
| 64 | 10 | 10 |
| 58 | 15 | 15 |
| 54 | 12 | 12 |
| 52 | 1 | 1 |
| 50 | 5 | 5 |
| ድምር | 100 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ የቀረበውን ስንመለከተው ንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ ውጤት ከፍተኛው የንባብ ፍጥነት ወይም ፈጣን አንባቢዎች ያስመዘገቡት 113 ቃላት በደቂቃ ሲሆን፣ ይህ ውጤት የተመዘገበው ከ100 ተማሪዎች መካከል በአስር ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ውጤት አንጻር ሲታይ 10% ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዝቅተኛው የንባብ ፍጥነት ወይም ዝግተኛ አንባቢዎች 50 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን ይህም በአምስት ተማሪዎች ወይም 5% የተመዘገበ ውጤት ነው፡፡

በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱ 100 ተማሪዎች መካከል 90 ከመቶው በደቂቃ ከ100 ቃላት በታች ያነባሉ፡፡ ይህም የንባብ ፍጥነታቸው ከክፍል ደረጃቸው አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ቀሪዎቹ 10 ከመቶ የሚሆኑት 113 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ ቢሆንም የንባብ ፍጥነታቸው ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ አማካይ በደቂቃ 67.99 ≈ 68 ቃላት ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ተማሪ በጣም ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 4.2.2. የተጠኚዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት

በአባሪ “3” ሠንጠረዥ ላይ በፍጥነት ንባብ ፈተና ሁለት የተመዘገበው ዝቅተኛ ሰአት 160 ሴኮንድ ወይም ፈጣን አንባቢዎች ምንባቡን አንብበው ለመጨረስ የፈጀባቸው ሰአት ሲሆን በተቃራኒው ከፍተኛ ሰአት ያስመዘገቡ ወይም ዝግተኛ አንባቢዎች 370 ሴኮንድ ፈጅቶባቸዋል፡፡ የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት መደበኛ ልይይት 46.36471577 ነው፡፡ የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተና ሁለት 394 ቃላትን የያዘ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ይህንን አንብበው የጨረሱበት ጊዜ ተመዝግቦ ተይዟል፡፡ ከዚያም ምንባቡ የያዘው የቃላት ብዛት አንበበው ለመጨረስ በፈጀው ጊዜ ተካፍሎ በስድስት ተባዝቶ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

ሠንጠረዥ 5፡ የተጠኝዎች የንባብ ፍጥነት በፈተና ሁለት

| የተጠኝዎች የማንበብ ፍጥነት በደቂቃ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| 148 | 3 | 3 |
| 139 | 5 | 5 |
| 131 | 7 | 7 |
| 99 | 3 | 3 |
| 91 | 20 | 20 |
| 88 | 27 | 27 |
| 84 | 19 | 19 |
| 79 | 5 | 5 |
| 70 | 9 | 9 |
| 66 | 1 | 1 |
| 64 | 1 | 1 |
| ድምር | 100 | 100 |

የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት ውጤት እንደሚያመለክተው 85 ከመቶ የሚሆኑት ተጠኝዎች ከ100 ቃላት በታች በደቂቃ ያነበቡ ሲሆን 15 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከ100 በላይ ቃላት በደቂቃ አንብበዋል፡፡ ከፍተኛ ቃላት በደቂቃ ያነበቡት ፈጣን አንባቢዎች 148 ቃላት በደቂቃ ሲሆን እነዚህም ሶስት ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህም ከአጠቃላይ ተጠኝ ተማሪዎች 3 ከመቶውን ብቻ ይይዛሉ፡፡ የንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት አማካይ ስንመለከት 89.51 ≈ 90 ቃላት በደቂቃ ያነባሉ፡፡ ይህ የሚያሳየን አብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት ያለው ወይም ዝግተኛ አንባቢ ቢሆንም የፍጥነት ንባብን ማሻሻል እንደሚቻል የሚያሳይ ነው፡፡

## 4.2.3. የፈተና አንድና ሁለት አማካይ የቃላት ብዛትና የማንበብ ፍጥነት

ሠንጠረዥ 6፡ የተጠኚዎች አማካይ የንባብ ፍጥነት የሚያሳይ መረጃ

| የምንባቦቹ አማካይ የቃላት ብዛት | ምንባቡን ለማንበብ የፈጀው ጊዜ በሴኮንድ | ድግግሞሽ | ጠቅላላ ድግግሞሽ |
|---|---|---|---|
| 367 ቃላት | 170 | 1 | 1 |
| | 175 | 1 | 2 |
| | 180 | 2 | 4 |
| | 190 | 1 | 5 |
| | 210 | 3 | 8 |
| | 215 | 1 | 9 |
| | 220 | 2 | 11 |
| | 225 | 2 | 13 |
| | 230 | 2 | 15 |
| | 235 | 3 | 18 |
| | 240 | 4 | 22 |
| | 245 | 2 | 24 |
| | 250 | 2 | 26 |
| | 255 | 2 | 28 |
| | 260 | 5 | 33 |
| | 265 | 2 | 35 |
| | 270 | 3 | 38 |
| | 280 | 4 | 42 |
| | 285 | 7 | 49 |
| | 290 | 8 | 57 |
| | 295 | 2 | 59 |
| | 300 | 5 | 64 |
| | 305 | 3 | 67 |
| | 310 | 7 | 74 |
| | 315 | 5 | 79 |
| | 320 | 1 | 80 |
| | 325 | 3 | 83 |
| | 330 | 7 | 90 |
| | 335 | 1 | 91 |
| | 340 | 2 | 93 |
| | 345 | 1 | 94 |
| | 360 | 4 | 98 |
| | 380 | 1 | 99 |
| | 390 | 1 | 100 |
| ድምር | 28,205 | 100 | 100 |
| መደበኛ ልይይት | 46.24318132 | | |
| አማካይ | 282.05 | | |

የተጠኚዎች ብዛት፡ 100

የምንባቡ አማካይ የቃላት ብዛት ፡ 367

ምንባቡን አንብቦ ለመጨረስ የፈጀው አማካይ ሰአት ፡ 282.05 ሴኮንድ

መደበኛ ልይይት፡ 46.24318132

በአጠቃላይ በሰንጠረዥ የተመለከተው የማንበብ ፍጥነት በ Nuttal ( 1982;36) ቀመር ሲሰላ የሚገኘው ውጤት 78.07 ነው፡፡ ይህም ተማሪዎቹ በአማካይ 78 ቃላትን በደቂቃ እንደሚያነቡ ያመለክታል፡፡

$$\frac{X}{Y} X6=z$$

$$\frac{367}{28.205} X6=Z$$

$$13.0118773X6=Z$$

$$Z= 78.071264 \approx 78$$

በሁለቱም የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን ስንመለከት በንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ 50 ቃላት በደቂቃ ያነበቡ አምስት ተማሪዎች ሲሆኑ በንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት ደግሞ 64 ቃላት በደቂቃ ያነበበው አንድ ተማሪ ነው፡፡ ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት ላይ የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ ቢመጣም እንኳ የንባብ ፍጥነቱ አሁንም ከሚፈለገው ደረጃ በታች እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሁለቱም የንባብ ፍጥነት ፈተናዎች ማለትም በንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና በንባብ ፍጥነት ፈተና ሁለት አማካይ የተመዘገበው ሰአት 282.05 ሴኮንድ ሲሆን በ Nuttal ( 1982) የስሌት ቀመር ሲሰላ የሚያሳየን አብዛኛው ተማሪ ወይም 87.5 ከመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት እንዳላቸው ሲሆን አብዛኛው ተማሪ የፍጥነት ንባብ ችግር እንዳለበት አመላካች ነው፡፡

## 4.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ጋር ያለው ግንኙነት

ከዚህ ጥናት ንኡሳን አላማዎች አንዱ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንጻር ማጥናት እንደሆነ በምዕራፍ አንድ ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሥራ ውስጥ የታቀፉት 25 ተማሪዎች አፋቸውን በኦሮሚኛ ቋንቋ የፈቱ፣ 25 ተማሪዎች አፋቸውን በኮንሲኛ ቋንቋ የፈቱ፣ 25 ተማሪዎች አፋቸውን በኮረቴ ቋንቋ የፈቱ እና 25 ተማሪዎች አፋቸውን በድራሽኛ ቋንቋ የፈቱ በአማርኛ ኢ. አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ተማሪዎች መካከል ያለውን የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አንጻር ለመመርመር ጥረት ተደርጓል፡፡ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 7 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከንባብ ፍጥነትና ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ግንኙነት

| የተጠኚ ተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ | በደቂቃ የሚያነቡት የቃላት ብዛት በአማካይ | አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ከ10% |
|---|---|---|
| ኦሮሚኛ | 78.5 ≈ 79 | 6.32 ≈ 6 |
| ኮንሲኛ | 75.1≈ 75 | 6.32≈6 |
| ኮረቴ | 78.4 ≈ 78 | 5.6≈ 6 |
| ደራሽኛ | 82.05 ≈ 82 | 6.38 ≈ 6 |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በጥናቱ ከተካተቱ 100 የ9ኛ ክፍል ኢአፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ አፋቸውን በደራሽኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በደቂቃ በአማካይ 82 ያህል ቃላትን ሲያነቡ፣ አፋቸውን በኦሮሚያ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ደግሞ 79 ቃላትን በደቂቃ አንብበዋል፡፡ በመቀጠል 78 ቃላትን በደቂቃ ያነበቡት አፋቸውን በኮረቴ ቋንቋ የፈቱት ሲሆን አፋቸውን በኮንሲኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ከሌሎች ባነስ በደቂቃ 75 ያህል ቃላትን አንብበዋል፡፡ ይህ የሚያሳየን በማንበብ ፍጥነት የተሻለ ደረጃ ላይ ያሉት አፋቸውን በደራሽኛ ቋንቋ የፈቱት ሲሆኑ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉት አፋቸውን በኮንሲኛ ቋንቋ የፈቱት እንደሆኑ አመላካች ነው፡፡ ነገር ግን እርስ በርስ ስናነጻጽራቸው ደረጃ ሰጠናቸው እንጅ አብዛኛው 87.5 ከመቶ የሚሆኑት


ተማሪዎች በደቂቃ ከመቶ ቃላት በታች ያነባሉ። ይህ የሚያሳየን የንባብ ፍጥነታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን ነው።

አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ስንመለከት Narayanswamy (1995:144-147) በገለጹት መሰረት ሁሉም ኢአፍ ፈት ተማሪዎች ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆናቸውን መረዳት እንችላለን። ነገር ግን ከቀረቡት ኢአፍ ፈቶች መካከል የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው በደራሽኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱት ሲሆኑ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡት ደግሞ በኮረቴ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

በአጠቃላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከንባብ ፍጥነት እና ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ግንኙነት ወደ ፊት በጥልቀት ለማጥናት የሚያስችሉ ፍንጮች ተገኝተውበታል።


## 4.4. የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ ግንኙነት

በሁለት የተለያዩ ተለዋዋጮች መካከል ያለውን የተዛምዶ አቅጣጫ ለማሳየት ግራፍ መጠቀም እንደሚቻል ያለው (1998:327-328) ያስረዳሉ። ለዚህም የንባብ ፍጥነት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታን በግራፍ ለማሳየት ተሞክሯል።



ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው በንባብ ፍጥነት ፈተና አንድ ፈጣን አንባቢዎች 340 ቃላትን በ180 ሴኮንድ ያነበቡ ሲሆኑ ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ በ510 ሴኮንድ አንብበዋል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና አንድ ውጤትን ስንመለከት ከፍተኛው 10 ከአስር ሲሆን ዝቅተኛው 2 ከአስር ነው፡፡ አስር ከአስር ውጤት የተመዘገበው በፈጣን አንባቢዎች ሲሆን 2 ከአስር የተመዘገበው በዝግተኛ አንባቢዎች ነው፡፡ በመሆኑም ለንባብ የፈጀው ሰአት ሲጨምር አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤቱ ይቀንሳል፤ ለማንበብ የፈጀነው ሰአት ሲቀንስ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ይጨምራል ማለት ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተደጋጋፊ መሆናቸውን ነው፡፡

## 4.5. የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ግንኙነት




የንባብ ፍጥነት

የንባብ ፍጥነትና የአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለትን ውጤት ከግራፍ እንደምንረዳው ፈጣን አንባቢዎች 394 ቃላትን በ160 ሴኮንድ ሲያነቡ ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ 370 ሴኮንድ ፈጅቶባቸዋል፡፡ በአንብቦ መረዳት ፈተና ሁለት ከፍተኛ ውጤት 10 ከአስር ሲሆን የተመዘገበውም በፈጣን አንባቢዎች ነው፡፡ ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ከአስር ከ1 እስከ 3 ያለውን ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በመሆኑም ፈጣን አንባቢዎች ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሲኖራቸው ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከሁለቱ ግራፎች መረዳት እንደሚቻለው በአንብቦ መረዳት እና በንባብ ፍጥነት መካከል ጠንካራ አሉታዊ ተዛምዶ መኖሩን ነው። በዚህም ለማንበብ የፈጀው ሰአት ሲቀንስ አንብቦ መረዳት ችሎታ ይጨምራል፤ ለማንበብ የፈጀው ሰአት ሲጨምር አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚቀንስ መሆኑን ነው።

## 4.6. በንባብ ፍጥነትና በአንብቦ የመረዳት መካከል ያለው ተዛምዶ

በንባብ ፍጥነት እና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለው ተዛምዶ በSPSS የኮንፒውተር ፕሮግራም በመጠቀም በባለሙያ ድጋፍ ተሰርቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ተቀምጧል።

ሠንጠረዥ 8፡ ንባብ ፍጥነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያሳይ

| | የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተና 1 | የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተና 2 | አማካይ |
|---|---|---|---|
| አንብቦ የመረዳት ፈተና 1 | -0.69749" | | |
| አንብቦ የመረዳት ፈተና 2 | | -0.74253" | |
| አማካይ | | | -0.73818" |

የተለያዩ ምሁራን በፍጥነት ንባብና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ጥብቅ ቁርኝት እንዳለ ገልጸዋል። የፍጥነት ንባብና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ቁርኝትም ውስብስብ ነው። ከዚህም የተነሳ ሁለቱ ንዑሳን ክሂሎች በአንድነት መዳበር እንዳለባቸው ያስረዳሉ።

Nuttal ( 2000:54) እና Anderson (1992:2) አንባቢዎች የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር በሚያደርጉት ጥረት የንባብ ፍጥነታቸውን በማሻሻል ብቁ አንባቢ ሊሆኑ እንደሚችሉና በፍጥነት ንባብና በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ትስስር እንዳለ ይገልጻሉ።

በዚህ ጥናታዊ ሥራም በእነዚህ በሁለቱ ንኡሳን የንባብ ክሂሎች መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል። በዚህም በተጠኝ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። በዚህም የተገኘው ውጤት -0.73818 እንደሆነ ታውቋል። ይህ የሚያሳየን በሁለቱም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መካከል ያለውን ዝምድናና የዝምድና ጥንካሬ ነው።

ከላይ የተገለጸው ውጤት -0.73818 በተማሪዎች የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ዝምድና ጠንካራ አሉታዊ ዝምድና ነው፡፡ ለማንበብ የሚፈጀው ሴኮንድ ሲጨምር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በእጅጉ ይቀንሳል፡፡ በተቃራኒው ለማንበብ የሚፈጀው ሴኮንድ ሲቀንስ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ይጨምራል፡፡ በሌላ አገላለጽ ፈጣን አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ሲሆን ዝግተኛ አንባቢዎች ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም የተማሪዎች የፍጥነት ንባብ ችሎታ ሲያድግ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውም አብሮ እንደሚያድግ ያሳያል፡፡

## 4.7. ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ሆኖ ያገለገለው ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በቃለ መጠይቁ የተሳተፉት የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ መረጃም በሚከተለው መልኩ በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ ( አባሪ “5”ን ይመልከቱ)፡፡

ሠንጠረዥ 9፣ ለቃለ መጠይቁ የተሳተፉ መምህራን አጠቃላይ መረጃ የሚያሳይ

| የመምህራን ብዛት | ጾታ | | የትምህርት ደረጃ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | | |
| 3 | 2 | 1 | ቢኤ ዲግሪ | 6-13 አመት |

ከሠንጠረዡ እንደምንረዳው ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን በቁጥር 3 ሲሆኑ 2 ወንድና አንድ ሴት ናቸው፡፡ የትምህርት ደረጃቸው የሁሉም ማለትም የሦስቱም ቢኤ ዲግሪ ነው፡፡ የአገልግሎት ዘመናቸው ደግሞ የመጀመሪያው 6 አመት፣ የሁለተኛው 13 አመት ሲሆን የሶስተኛዋ ደግሞ 9 አመት ነው፡፡

### 4.7.1. የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታንና የንባብ ፍጥነትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከመምህራን በቃለ መጠይቅ አማካይነት የተገኘው ምላሽ በፈተና አማካይነት የተገኘውን ውጤት የሚደግፍ ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው? ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው? ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ያውቃሉ? ከፈጣንና ከዝግተኛ አንባዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው? ተብለው

ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን ምላሽ ሲሰጡ ሶስቱም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነና ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችግር እንዳለባቸው ጠቅሰው ችግሩ የመነጨው ከታችኛው ክፍል ጀምሮ ፊደል ለይቶ አለመምጣት፣ ተማሪው በግል የንባብ ችሎታውን ለማዳበር ጥረት ያለማድረግ እና በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርትን በተገቢው መንገድ ለመስጠት የጊዜ እጥረት እንዳለ ገልጸዋል፡፡ ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ለማወቅ ያደረጉትን ጥረትን በተመለከተ ሁለቱ ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ለማወቅ ያደረጉት ጥረት እንደሌለና ፈጣን አንባቢው ከዝግተኛ አንባቢው የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው ለማለት ቢከብድም ባላቸው ልምድ ግን ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች አንድን ምንባብ አንብበው የመረዳት ችሎታ አላቸው በማለት መልሰዋል፡፡

አንድ መምህር ግን ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይቶ ማወቅ እንደቻለ ገልጾ ፈጣን አንባቢ የተባሉት በደቂቃ እስከ 121 ቃላትን ማንበብ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ችያለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ በዚህም የፈጣንና የዝግተኛ አንባቢዎችን የአንብቦ መረዳት ስለካ ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው መሆናቸውን ለማወቅ ችያለሁ በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም ከፈተና በተገኘው ውጤት ያረጋገጠችው የፈጣን አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከዝግተኛ አንባቢዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ የተሻለ መሆኑን ነው፡፡

### 4.7.2. በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ ለማወቅ የሚከተሉት መጠይቆች ለመምህራን ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንባብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት ባለ ዘዴ ነው? የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ስራዎች አሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች መምህራኑ ምለሽ ሲሰጡ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የተለያዩ ምንባቦችን እንዲያነቡ የሚደረገው በዝምታ የማንበብ ስልት ነው በማለት የገለጹት ሁለት ናቸው፡፡

በዝምታ እንዲያነቡ የሚደረግበትን ምክንያት ሲገልጹ የተለያዩ ምሁራን እንደገለጹት በፍጥነት የማንበብ ስልትን ለመጨመር ብሎም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የጮክታ ንባብ ስልትን ሳይሆን የዝምታ ንባብ ስልትን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው በማለት

ይገልጻሉ፡፡ አንድ መምህር ግን በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የተለያዩ ምንባቦችን ድምጽ አሰምተው እንዲያነቡ ከተደረገ በኂላ መምህሩ ደግመው እንደሚያነቡ ገልጸው ምክንያቱን ሲያብራሩ ተማሪው ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲያነብ መምህሩ የተማሪውን ትክክለኛነት፣ ተገቢ አገላለጽ ወዘተ. እየተከታተለ እርማት እንደሚሰጥ እና መምህሩ እራሱ ደግሞ ሲያነብ ተማሪው የራሱን ስህተት ሊያርም እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማወቅ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ ሁሉም መምህራን ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ከማሰራት በዘለለ በትምህርት ቤት ደረጃ የተለየ ስራ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ በፈተና አማካይነት የተገኘው የአንብቦ መረዳት ውጤት ከመምህራን ሀሳብ ጋር ተዛማጅነት ያለው ሆኖ እናገኛለን፡፡

### 4.7.3. የመምህራን ክትትልና የራስ ጥረትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንትና

ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ያዳብሩ ዘንድ መምህራን ምን አይነት ክትትል እንደሚያደርጉ ለማወቅ ለመምህራን የሚከተሉት መጠይቆች ቀርበውላቸዋል፡፡ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? በሚል ለመምህራን ቃለ መጠይቅ የቀረበ ሲሆን ከሁሉም ተጠያቂ መምህራን የተገኘው ምላሽ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ብለው ሌሎች ምንባቦችን ሲያነቡ አይስተዋሉም፡፡ በመሆኑም ፍጥነታቸውም ሆነ ልምዳቸው አነስተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን መደረግ አለበት? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሲሸጋገሩ በቂ የሆነ የንባብ ችሎታ ይዘው እንዲመጡ ቢደረግ፣ በንባብ ትምህርት ጊዜ ለተማሪዎች ተገቢ ድጋፍና ክትትል ቢደረግ፣ ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክፍለ ጊዜ አናሳ በመሆኑ ማሻሻያ ቢደረግ እና በንባብ ሂል ላይ ለመምህራን ተከታታይነት ያለው ስልጠና ቢሰጥ በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽና በዋና የመረጃ መሰብሰቢያው ፈተና አማካይነት የተገኘው ውጤት የሚያሳየው አብዛኛው ተማሪ ዝግተኛ አንባቢ እንደሆነና ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው መሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በሠገን አካባቢ ሕዝቦች ዞን በሠገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት አማርኛ ኢ አፍ ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ያለውን ዝምድና መፈተሽ ሲሆን ዝርዝር አላማዎችም እንዳሉት በምዕራፍ አንድ ተገልጿል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ስለ ንባብ ምንነት፣ ስለአንብቦ መረዳት ችሎታ ምንነት፣ ስለ ፍጥነት ንባብ ምንነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍጥነት ንባብ ጋር ያለውን ተዛምዶ ምሁራን ያነሷቸውን ሀሳቦችና ያደርጓቸውን ጥናቶች በማስደገፍ ተዘርዝሯል፡፡ በምዕራፍ ሶስት ደግሞ ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የቀረበው ፈተና፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃና መረጃው እንዴት እንደሚተነተን በዝርዝር ቀርቧል፡፡

በምዕራፍ አራት ደግሞ በፈተና የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖ ውጤቱ የተገለጸ ሲሆን ከዚህ ውጤት በመነሳት የሚከተለው የማጠቃለያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

አብዛኛው ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታው ዝቅተኛ ወይም ከሚጠበቀው ደረጃ በታች መሆኑን ማወቅ ተችሏል፡፡ ማለትም ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተጠኚ ተማሪዎች ከአስር ከታረመ ፈተና ከ5-6 እና ከ5 በታች ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህ የሚያሳየን አብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳለው ነው፡፡

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት አብዛኛው ተማሪ ( 55.5%) ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያመለክት ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የንባብ ፍጥነታቸውም በጣም ዝቅተኛ ከመቶ ቃላት በታች ነው፡፡ በአንጻሩ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች የንባብ ፍጥነታቸውም ከዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ የሚያሳየን በአንብቦ መረዳትና በፍጥነት ንባብ መካከል ዝምድና መኖሩን ነው፡፡

የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነት ለማወቅ በተሰጠው ፈተና ተማሪዎቹ በአማካይ በደቂቃ 78 ያህል ቃላት እንደሚያነቡ የታወቀ ሲሆን የማንበብ ፍጥነታቸው ከክፍል ደረጃቸው አንጻር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል።

ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ያላቸው የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው።

ለዚህም

- ተማሪዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሲሸጋገሩ ተገቢውን የንባብ ችሎታ ይዞ አለመምጣት
- ተማሪዎቹ የራሳቸውን የንባብ ልምድ ለማሻሻል ጥረት ያለማድረግ
- በቂ የልምምድ ጊዜና ተገቢ ድጋፍ ያለመኖር ይጠቀሳሉ።

በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋና በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት መካከል ያለውን ግንኙነት ስንመለከት የተሻለ የንባብ ፍጥነት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ሆነው የተገኙት አፋቸውን በደራሽኛ ቋንቋ የፈቱት ሲሆኑ ቀጥሎ አፋቸውን በኦሮምኛ እና በኮረቴ ቋንቋ የፈቱት በሁለተኛ እና በሶስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡ ሲሆን ዝቅተኛ የንባብ ፍጥነት ያላቸው አፋቸውን በኮንስኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች እንደሆኑ አመላካች ነው። ነገር ግን የንባብ ፍጥነታቸውም ሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ ታውቋል።

## 5.2. አስተያየት

የጥናቱ አቅራቢ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ የሚሉትን የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰንዝራለች። ንባብ በትምህርት መማር ማስተማር ውስጥ ዋነኛው መሳሪያ ነው። በመሆኑም ለማንበብ መማር፣ ለመማር ደግሞ ማንበብ ያስፈልጋል። ከዚህ በሻገር ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም የዕለት ተዕለት ህይወታቸውን የተሳካ ለማድረግ አለም ከደረሰበት የስልጣኔ ደረጃ ለመድረስ ንባብን መሳሪያ ማድረግ ተገቢ ነው። የንባብ ስልታችንም በፍጥነት ማንበብና አንብቦ መረዳትን በሚያዳብር መልኩ ቢሆን ውጤታማ ያደርገናል። ከዚህ ጥናትም የምንገነዘበው ይህንኑ ነው። በመሆኑም

1. መምህራን ተማሪዎች የንባብ ልማዳቸውን እንዲያጎለብቱ በክፍል ውስጥ ከሚማሩት ውጪ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻሕፍት ገብተው ሌሎች ምንባቦችን እንዲያነቡ ቢያበረታቷቸው፡፡
2. የተማሪዎችን በአማርኛ አንብቦ የመረዳትና የንባብ ፍጥነት ለማሻሻል የሚያግዙ የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች ተግባራዊ የሚደረጉበት ሁኔታ ቢመቻችና ለንባብ ክሂል ትኩረት ቢሰጥ ፤
3. ለመምህራን በማንበብ ክሂል ላይ በጥልቀት ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ ተከታታይ ስልጠና ቢሰጥ፤
4. የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ሲዘጋጁ አንብቦ የመረዳት ችሎታን በሚያዳብር መልኩ፣ የፍጥነት ንባብ ስልትን ተግባራዊ እንዲሆን በሚያደርግ መልኩ የሚዘጋጅበት ስልት ቢቀየስ፤
5. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ ስላልሆነ የሚስተካከልበት ሁኔታ ቢፈጠር፣
6. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከአንብቦ መረዳት ችሎታና ከንባብ ፍጥነት ጋር ያለውን ተዛምዶ ወደፊት በጥልቀት ቢጠና የተሻለ ለውጥ ይመጣል የሚል እምነት አላት፡፡

# ዋቢዎች


መኮንን ናና (2000)፡፡ "በአዊኛ አፋቸውን የፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ግምገማ፡፡" ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ (1997)፡፡ "በካምባታ ጠምባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ፍጥነታቸው፡፡" ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ትምህርት ሚኒስተር (2007)፡፡ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህራን ማሰልጠኛ ማንዋል፡፡ አዲስ አበባ፣ ትህምርት ሚኒስተር

አለም እሸቱ /1995/፡፡ 'በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር፡፡" ከጥቅምት 25 እስከ 29/1995 ዓ.ም ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ2ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ ከስ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፣ አዲስ አበባ፡፡

_______ (1997)፡፡ "ንባብ፣አንብቦ የመረዳት እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ፡፡" አዲስ አበባ፣ ( ያልታተመ)፡፡

አያሌው አንተነህ (2001) "በአማርኛ ቋንቋ የፍጥነት ንባብ ክሂል ከአንብቦ መረዳት ክሂል ጋር ያለው ተዛምዶ፡- በወልዲያ የከፍተኛ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ ጥናት፡፡" ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ (1998)፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡* ባህርዳር፣ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

Alderson, J.and Urguhart,A.(eds). (1984) *Reading in a Foreign Language*. New York: Longman.

Alderson, J.C (2000). *Assessing Reading. Cambridge*: Cambridge University Press.

Anderson,N.J.(1999) " Improving Reading Speed Activities For Classroom" *English Teaching Forum* vol.37,no.2 april.anderson,r.c. etal.(1988).Growth in Reading and How Children Spend their Time Outside of School.Reading Research Quarterly,23(3).pp.285-303.http/www.tureboread.com/

Bell,T.(2001). "Extensive Reading Speed and Comprehension." The Reading Matrix, vol. 1, No. 1, April. http : // *www. Reading Matrix.com*/ Articles /bell/ indexhtml.

Fry, E. (1963) *Reading Faster: A Drill Book.* Cambridge: Cambridge University press.

Grabe,W.and L.F.Stoller.(2002).*Teaching and Researching Reading*. Hariow: Pearson Education.

Greenwood,J.(1981). "Compensation and Reading". In Abbott,g.and Wingard,P.(eds) *Teaching of English as an International Language: A practical Guide*.Oxford; Oxford University Press.

Grellet,F.(1981) *Developing Reading Skills*: *A Practical Guide to Reading comprehensive Exercise* (1st ed.).Cambridge: Cambridge University Press.

--------(1996).*Developing Reading Skills*. Cambridge:CambridgeUniversity Press.

Heaton,J.B.(1975). *Writing Language Tests*: *A Practical Guide for Teachers of English as Second Language Foreign Language*. London: Longman.

--------------(1991). *Writing English Language Testing*. New York: Longman Inc.

Hughes,A.(1989). *Testing for Language Teachers*. Cambridge: Cambridge University Press.

Lage,B.(1981). " Making Sence with Schemata" *Journal of Reading* 24(5): 442-445.

Lindsay and Knight (2006) *Learning and Teaching English*. Oxford: Oxford University Press.

Madsen,H.S.(1983).*Techniques in Testing*. New York: Oxford University Press.

May.F.B.(1990). *Reading as Communication in an Interacting Approach (3rd ed.)*. New York: Merill Publishing Company.

Narayanaswamy, K.R. ( 1975) *"The Measurement of Reading Ability". ELT Journal* 29 (2) 144-147.

Nelson, H. (1963). " Overcoming Reading Deficiencies at the College Level." *Journal of Developmental Reading*. Vol.6, P.P 238.

Nuttal, C. (1982).*Teaching Reading Skills.* Cambrdige: Cambridge University Press.

----------(2000).*Teaching Reading Skills for in a Foreign Language*. London: Henemann Educational Books.

Perfetti, C.A. (1985). *Reading Ability*. Oxford: Oxford University Press.

Sheng, H.S (2000). " A Cognitive Model for Teaching Reading Comprehension." *English Teaching Forum* Vol. 38, No.4, October.

Weier,C.J. ( 1990) *Communicative Language Testing.* London: Prentice - Hall.

Williams,E.(1984).*Reading in the Language Classroom*. London: Macmillan Publishing.

------------(1990).*Reading in the Classroom*. London: Macmillan Publishers,Ltd.

# አባሪ አንድ

የፍጥነት ንባብ እና የአንብቦ መረዳት ፈተና አንድ

ስም--------------------------

የአፍ መፍቻ ቋንቋ------------------------

**አጠቃላይ መግለጫ፣**

የዚህ ፈተና ዓላማ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ስለሆነም ምንባቡን በተቻለ መጠን በተለመደው ፍጥነታችሁ በጥንቃቄ አንብባችሁ ከምንባቡ ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

**ምንባብ አንድ**

**" ቀድሜ እንድበላ"**

የሰው ልጅ ከፍጥረታት ሁሉ ብልህና አርቆ አሳቢ ነው፡፡ ከጥንት የጋርዮሽ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ ፈጠራዎችን ሲጠቀም ኖሯል፡፡ በቤቱ ውስጥ እንስሳትን እያላመደ ያቆያል፡፡ ነገርግን አንድ ለማዳ ሳትሆን በቤት ውስጥ የምትተራመስ ጎጆዋን በሰውጎጆ ቀልሳ የምትኖር እንስሳን ጨርሶ ማራቅ አልቻለም፡፡ ብዙዎቹ ስሟን እንኳን ለመጥራት ሲቀፋቸው ይስተዋላል፡፡ "አይጥ" በእንሊዘኛው አጠራር mouse ወይም rat አፈጣጠሯ ከአጥቢ እንስሳት መካከል ትመደባለች፡፡ እንዲሁም በፈጣን እንቅስቃሴዋ እና በማሽተት ችሎታዋ ከፍተኝነት ትታወቃለች፡፡

የአይጥ አማካኝ እድሜ 18 ወራት ሲሆን በርካታዎቹ ግን በተለያየ ምክንያቶች አንድ አመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ፡፡ አይጥ በአብዛኛው በእንጨትና ከአፈር በተሰሩ ቤቶች ውስጥ በቀላሉ ገብታ ለመኖር የሚያስችላትን ጠንካራ ጥርስም ታድላለች፡፡ አንዳንዴም በድንጋይና በብሎኬት በተሰሩ ቤቶች ውስጥ ከገባች ዘሮቿን በማብዛት ተደላድላ ለመኖር አትቸገርም፡፡

እናም በኢትዮጵያ ደግሞ አብዛኛው ቤቶች የተሰሩት ከአፈርና ከእንጨት በመሆኑ በእያንዳንዱ ጓዳውስጥ አለች ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ አለቃገብረሃናም ምግብ በሚበሉበት ቤት ውስጥ ትንሽዋ እንስሳን ከእንጀራ ማስቀመጫው መሶብ ስር በማየታቸው

“ከመሶብ አይጡ” ብለው የመረቁ መስለው ከመሶቡ ስር አይጥ ማየታቸውን አመስጥረው መናገራቸውን ታሪክ ይናገራል፡፡ ነገሩ ጥንትም ትንሿ እንስሳ እንደድመት ከሰዎች ጋር ተላምዳ ቤት ውስጥ እንድትኖር አይፈቀድላት እንጂ በእያንዳንዱ ቤት ጓዳ ጎድጓዳ የመገኘቷ ጉዳይ አጠራጣሪ አይደለም፡፡ ያለፈቃድ በቤት ውስጥ የመገኘቷ ጉዳይም ብዙዎችን ሲያንገበግባቸው ይኖራል፡፡

በተለይ የሰፈራችን ዕድሜ ጠገብ ልብስ ሰፊ  አቶ አክሊሉ እንስሳዋን ክፉኛ አይወዷትም፡፡ በአንድ ወቅት በቤታቸው ራዲዮናቸውን ከፍተው አረፍ ባሉበት ወቅት ከዘራቸው ላይ ተጠምጥማ ስታበቃ  ወደ ጉድጓዷ የገባችበት ጊዜ ለእርሳቸው እንደ ህልም ነው የሚታወሳቸው፡፡ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ላገኙት ሰው ሁሉ “ ይቺ ከይሲ ፍጥረት ከዘራዬን አረከሰችው” እያሉ ለለቅሶና ለጥየቃ በሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ ሲያንቋሽሿት ይውላሉ፡፡ “ አይጥ” ብለው  እንኳን ደፍረው መጥራት ስለማይሆንላቸው “ስሚን ቁስ ይጥራውና” እያሉ ነው ወጋቸውን የሚጠርቁት፡፡ እና በየእለቱ ወጥመድ ቢያዘጋጁም፣ መርዝ ቢነሰንሱ የተወሰኑትን ይገድላሉ እንጂ ጭራሽ ልትጠፋ አልቻለችም፡፡ አዳኝ የተባሉ ድመቶችን በቤታቸው ውስጥ ቢያሰማሩም ድመቶች ከመንደር በሚቃርሙት ትርፍራፊ ሆዳቸውን ቀብትተው የቤቱ እድሜ ጠገብ ሶፋ ላይ መገላበጡን ተያይዘውታል፡፡

አንድቀን ታዲያ አዛውንቱ ከስራ ወደ ቤታቸው ገብተው አረፍ እንዳሉ ባለቤታቸው ምግብ ለማቅረብ መሶቡን ከፈት ቢያደርጉት አጂሪት ተስፈንጥራ ወጥታ በአልጋቸው ውስጥ ተደበቀች፡፡ አቶ አክሊሉ የዛን ቀን እህል አልበላም ብለው እስከ ምሽቱ ሶስት ሰአት ድረስ ሲግደረደሩ ቆይተው ደረቅ ዳቦ አስገዝተው ተመገቡ፡፡

አቶ አክሊሉ ነገሩ የከነከናቸው “ እርሳቸው ያልበሉትን እንጀራ እንዴት አይጧ ቀድማ ትመገበዋለች” የሚለው መበለጥ ነበር፡፡ ባለቤታቸው ደግሞ “ የዛሬን ነው እንዴ አይጧ ሁሌስ ሽር የምትለው ከመሶብ አይደል እንዴ” ብለው ንዴታቸውን የሚያባብስ ንግግር አከሉላቸው፡፡

(ምንጭ፡- አዲስ ዘመን ጋዜጣ 77ኛ ዓመት፣ ቁጥር099፣ ሰኞ ታህሳስ 9ቀን 2010 ዓ.ም)

ስም ________________

አፍ መፍቻ ____________

I. **የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ “ እውነት” ትክክል ከልሆነ “ ሐሰት” በማለት ጻፉ፡፡**

______1. አይጥ ከአጥቢ እንስሳት መካከል ትመደባለች፡፡

______2. ከጥንት ጀምሮ አይጥ እንደድመት ለማዳ እንስሳ ሆና በቤት ውስጥ ትኖራለች፡፡

______ 3. አይጥ በድንጋይና በብሎኬት በተሰራ ቤቶች ውስጥ መግባት አትችልም፡፡

______ 4. የሰው ልጅ ከፍጥረታት ሁሉ ብልህና አርቆ አሳቢ ቢሆንም እስከ አሁን አይጥን ከራሱ ማራቅ አልቻለም፡፡

______5. ድመቶች አይጧን መያዝ ያልቻሉት ከመንደሩ በሚቃርሙት ትርፍራፊ ሆዳቸውን ስለሚሞሉ ነው፡፡

II. **ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

______ 6. የአይጥ አማካኝ ዕድሜ ምን ያህል ነው?

ሀ. 18 ዓመት ለ. 18 ወራት ሐ. 1 ዓመት መ. 2 ዓመት

______ 7. በኢትዮጵያ አብዛኛው ቤቶች የተሰሩት ከምንድን ነው?

ሀ. ከብሎኬት ለ. ከድንጋይ ሐ. ከአፈርና ከእንጨት መ. ከድንጋይና ከእንጨት

______8. አቶ አክሊሉ “ ስሟን ቄስ ይጥራው” ያሉት ማንን ነው?

ሀ. ባለቤታቸውን ለ. ከዘራቸውን ሐ. ድመታቸውን መ. አይጧን

______ 9. አይጥ ከፈጣን እንቅስቃሴዋ በተጨማሪ በምን ትታወቃለች?

ሀ. በማሽተት ችሎታዋ ከፍተኛነት ሐ. በማየት ችሎታዋ ከፍተኛነት

ለ. በማድመጥ ችሎታዋ ከፍተኛነት መ. በመቅመስ ችሎታዋ ከፍተኛነት

______ 10.አቶ አክሊሉ እህል አልበላም ብለው እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ድረስ የቆዩት በምን ምክኒያት ነው?

ሀ. እሳቸው ያልበሉትን እንጀራ አይጧ ቀድማ በመመገቧ
ለ. ከባለቤታቸው ጋር በመጣላታቸው፡፡
ሐ. እንጀራ መብላት ስላልፈለጉ
መ. አይጧ አልጋቸው ላይ በመውጣቷ

## አባሪ ሁለት

## የፍጥነት ንባብ እና አንብቦ የመረዳት ፈተና ሁለት

ስም--------------------------

የአፍ መፍቻ ቋንቋ-----------------------

**አጠቃላይ መግለጫ፣**

የዚህ ፈተና ዓላማ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ስለሆነም ምንባቡን በተቻለ መጠን በተለመደው ፍጥነታችሁ በጥንቃቄ አንብባችሁ ከምንባቡ ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

ምንባብ ሁለት

ጓያ ሲበላ በዕውቀት

በሳይንሳዊ ስሙ (Lathyrus sativus)እየተባለ የሚጠራው ጓያ፣ የተለያየ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን ማለትም ጎርፍ፣ ድርቅና በሽታን ተቋቁሞ መብቀል ይችላል፡፡ በእርግጥ ተመሳሳይ የሆኑ ብዙ ዝርያዎች አሉት፡፡ ተክሉ በኢትዮጵያ ውስጥ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በሸዋ፣ በወሎና በትግራይ ይበቅላል፤ ለምግብነት ጥቅምም ይውላል፡፡ ይህ ተክል በመሬት ላይ የናይትሮጂን መጠን በመጨመር የአፈር ለምነትን እንደሚጨምር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ጓያ ከፍተኛ ካርቦሃይድሬትና የፕሮቲን ምንጭ ነው፡፡ ከክብደቱ 58% የሚሆነው ካርቦሃይድሬት 25% ደግሞ ፕሮቲን ሲሆን ዝቅተኛ የቅባት ይዘትና ከፍተኛ የካልሽየምና የፎስፈረስ ማዕድናትን በውስጡ ይዟል፡፡

የጓያ ተክል መርዛማ ተክል ሲሆን በተደጋጋሚ መመገብ ከወገብ በታች የነርቭ ስርአትን የሚያዛባ በሽታ(neurolathyrism) ያስከትላል፡፡ መርዛማነቱ በተለያየመጠን በተደጋጋሚ ወደሰውነታችን ከገባ በአንጎላችንና በህብለ ሰረሰራችን ውስጥ በመከማቸትና የነርቭ ስርአታችንን በማዛባት ከወገብ በታች ሽባነትን ያስከትላል፡፡ ጓያን ለአንድ ወይምን ለሁለት ሳምንታት በተከታታይ መመገብ አልያም ከዕለታዊ የምግብ ፍጆታ ሲሶውን(1/3) መመገብ ከወገብ በታች ያለውን አካል በማሽመድመድ ሽባ እንደሚያደርግ ይነገራል፡፡

የጓያ ተክል ፍሬውን ስንመገብ በውስጡ የሚገኘውን ኦዳፕ የተባለው መርዛማ ኬሚካል ውህድ ከወገብ በታች ያለው አካል ላይ መሽመድመድ ሊያስከትል ይችላል፡፡

አንድ ሰው ይህንን ተክል በመመገብ ለበሽታው የሚጋለጠው በቅጽበት አልያም በአዝጋሚ ሁኔታ ስለሚሆን ሕመሙ እንደጀመረ የጡንቻና የጅማት መሸማቀቅ ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና ስር እየሰደደ በመሄድ ተጠቂው በድንገት መንቀሳቀስ ያቅተዋል፡፡ የተደረጉ አንዳንድ ሳይንሳዊ ምርምሮች እንደሚያብራሩት የህመም ምልክቶች በሚከተሉት ሁኔታ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

- ቅጽበታዊ የሆነ የጡንቻ መሸማቀቅ ስሜት በእግር ላይና ባት አካባቢ ይሰማል፣
- በባት ላይ አነስተኛ እብጠት ይኖራል፣
- በጭንና በታፋላይ የህመምስሜት ይፈጥራል፣
- የእግር አውራጣትና መዳፍ በቀላሉ አልታዘዝም ይላል፣
- የእግር ጡንቻዎች ላይየህመም ስሜት ይከሰታል፡፡

ይህ የገጠማቸው ሰዎች በታችኛው የጭናቸው ክፍል ላይ የጡንቻ መጨማደድ፤ በተረከዝ ሙሉ በሙሉ መርገጥ አለመቻል የመጀመሪያ ደረጃ የጓያ ስብራት ምልክት ሲሆኑ በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኙ ህሙማን ያለድጋፍ መንቀሳቀስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ደረጃው ከፍ እያለ ሲሄድ የጡንቻ መጠንከርና አለመታዘዝ፤ የሰውነት ሚዛንን መጠበቅ አለመቻል በማስከተል ያለድጋፍ መንቀሳቀስ ሁሉ እስከ መከልከል ሊያደርስ ይችላል፡፡

ዋነኛ የጓያ ስብራት መከላከያ መንገድ ጓያን ለመግብነት ከመዋሉ በፊት በውስጡ የያዘውን አደገኛ መርዛማ ንጥረነገር በተለያዩ ዘዴዎች ማስወገድ ነው፡፡ ለአብነት በፈላ ውሃ መዘፍዘፍ አንዱ መንገድ ነው፡፡ ከሚዘፈዘፈው ጓያ በአራት እጅ የሚበልጥ ውሃ አፍልቶ ለሰአታት መዘፍዘፍና ደጋግሞ በቀዝቃዛ ውሃ እያጠቡ መርዛማ ንጥረነገሩን አስወግዶ በፀሐይ ማድረቅ፡፡

አልያም ጓያውን በቀዘቀዘ ውሃ ውስጥ ለ12ሰዓታት ያህል በመዘፍዘፍ ውሃውን በማስወገድ እርጥቡን የጓያ ፍሬ በእንፋሎት ከ20 እስከ 30 ደቂቃ ማፈን ከዚያም በቀዝቃዛ ውሃ ለአንድ ሰዓት ያህል መዘፍዘፍ፤ ከዚያም ውሃውን ማጥለልና በፀሐይ ማድረቅ፡፡ ሁለቱ ዘዴዎች በጓያውስጥ የሚገኘውን ከ80-90 የሚሆነውን መርዛማ ንጥረነገር ለማስወገድ እንደሚያስችሉ ከመረጃ ታውቋል፡፡

በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ጓያ በእንጀራ መልክ እየተዘጋጀ ብዙ ሰው ይመገበዋል፡፡

- በህክምና ስለማይድን የችግሩ ተጠቂዎች የእድሜልክ አካል ጉዳተኞች ይሆናሉ፡፡
- ኢትዮጵያን ጨምሮ ምስራቅ አፍሪካ፣ ቻይና፣ ህንድና ባንግላዲሽ የችግሩ ተጋላጭ አገሮች እንደሆኑ ካነበብነው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

( ምንጭ፡- ደቡብ ንጋት ጋዜጣ 20ኛ ዓመት፣ ቁጥር 536፣ ቅዳሜ ታህሳስ 21/2010ዓ.ም)

ስም ____________________

አፍ መፍቻ ______________

I. **የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ “እውነት” ትክክል ካልሆነ “ሐሰት” በማለት ጻፉ**

_______ 1. ጓያን በተከታታይ ለአንድ ወይም ለሁለት ሳምንት መመገብ ከወገብ በታች ያለውን አካል በማሽመድመድ ሽባ ያደርጋል፡፡

_______ 2. ጓያ በውስጡ ከፍተኛ የቅባት ይዘት አለው፡፡

_______ 3. ዋነኛው የጓያ ስብራት መከላከያ መንገድ ጓያን ለምግብነት ከማዋል በፊት በውስጡ የያዘውን አደገኛ መርዛማ ንጥረነገር በተለያየ ዘዴ ማስወገድ ነው፡፡

_______ 4. በጓያ ስብራት የተጠቁ ሰዎች በህክምና ይድናሉ፡፡

_______ 5. በአገራችን በሰሜኑ ክፍል ጓያ በእንጀራ መልክ እየተዘጋጀ ብዙ ሰው ይመገበዋል፡፡

II. **ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ ብቻ ምረጡ**

_______ 6. የጓያ ተክልን በተደጋጋሚ መመገብ የምን በሽታን ያስከትላል?

ሀ. የጉበት በሽታ ሐ. ከወገብ በታች የነርቭ ስርአትን የሚያዛባ

ለ. የአዕምሮ በሽታ መ. የልብ የደምዝውውርን የሚያዛባ

_______ 7. ከሚከተሉት ውስጥ የጓያ ስብራት የህመም ምልክት <u>ያልሆነው</u> የቱ ነው?

ሀ. የጡንቻና የጅማት መሸማቀቅ ሐ. የእግር አውራጣትና መዳፍ አለመታዘዝ

ለ. በባት ላይ እብጠት መኖር መ. ከፍተኛ የሆነ ትኩሳት

_______ 8. በጓያ ምክንያት ለሚፈጠረው ሽባነት ተጋላጭ የሆኑ ሀገሮች እነማን ናቸው?

ሀ/ ኢትዮጵያ ለ/ ምስራቅ አፍሪካ ሐ/ ቻይና መ/ ህንድ ሠ/ ሁሉም

_______ 9. በጓያ ተክል ፍሬ ውስጥ የሚገኘው መርዛማ ኬሚካል-------- ይባላል፡፡

ሀ. ካልሽየም ለ. ኦዳፕ ሐ. ፎስፈረስ መ. ካርቦሃይድሬት

_______ 10. ጓያ ከምግብነት ውጭ ምን ጥቅም አለው?

ሀ. የአፈርን ለምነት ይጨምራል ሐ. ዘይት ይዘጋጅበታል

ለ. ለማደዳበሪያነት ያገለግላል መ. ጎርፍን ይከላከላል

## አባሪ ሶስት

### ሠንጠረዥ 1፡ የንባብ ፍጥነት ፈተና አንድና ፈተና ሁለት ዝርዝር መረጃ

| | የንባብ ፍጥነት መለኪያ ፈተናዎች | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ፈተና 1 | ፈተና 2 | አማካይ |
| 1 | ኦሮምኛ | 210 | 170 | 190 |
| 2 | ›› | 300 | 260 | 280 |
| 3 | ›› | 210 | 270 | 240 |
| 4 | ›› | 180 | 240 | 210 |
| 5 | ›› | 380 | 280 | 330 |
| 6 | ›› | 350 | 280 | 315 |
| 7 | ›› | 300 | 360 | 330 |
| 8 | ›› | 390 | 260 | 325 |
| 9 | ›› | 380 | 280 | 330 |
| 10 | ›› | 410 | 180 | 295 |
| 11 | ›› | 180 | 340 | 260 |
| 12 | ›› | 300 | 280 | 290 |
| 13 | ›› | 260 | 270 | 265 |
| 14 | ›› | 350 | 280 | 315 |
| 15 | ›› | 380 | 340 | 360 |
| 16 | ›› | 300 | 300 | 300 |
| 17 | ›› | 510 | 270 | 390 |
| 18 | ›› | 380 | 180 | 280 |
| 19 | ›› | 300 | 270 | 285 |
| 20 | ›› | 180 | 170 | 175 |
| 21 | ›› | 260 | 340 | 300 |
| 22 | ›› | 350 | 260 | 305 |
| 23 | ›› | 260 | 260 | 260 |
| 24 | ›› | 300 | 270 | 285 |
| 25 | ›› | 260 | 260 | 260 |
| 26 | ኮንስኛ | 260 | 260 | 260 |
| 27 | ›› | 320 | 170 | 245 |
| 28 | ›› | 300 | 170 | 235 |
| 29 | ›› | 180 | 280 | 230 |
| 30 | ›› | 320 | 300 | 310 |
| 31 | ›› | 350 | 370 | 360 |
| 32 | ›› | 380 | 270 | 325 |
| 33 | ›› | 300 | 280 | 290 |
| 34 | ›› | 410 | 260 | 335 |
| 35 | ›› | 210 | 260 | 235 |
| 36 | ›› | 380 | 180 | 280 |
| 37 | ›› | 350 | 280 | 315 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 38 | ›› | 260 | 340 | 300 |
| 39 | ›› | 300 | 270 | 285 |
| 40 | ›› | 350 | 270 | 310 |
| 41 | ›› | 480 | 280 | 380 |
| 42 | ›› | 300 | 300 | 300 |
| 43 | ›› | 260 | 270 | 265 |
| 44 | ›› | 380 | 280 | 330 |
| 45 | ›› | 320 | 260 | 290 |
| 46 | ›› | 410 | 270 | 340 |
| 47 | ›› | 350 | 260 | 305 |
| 48 | ›› | 210 | 270 | 240 |
| 49 | ›› | 320 | 260 | 290 |
| 50 | ›› | 300 | 260 | 280 |
| 51 | ኮረቴ | 180 | 160 | 170 |
| 52 | ›› | 240 | 260 | 250 |
| 53 | ›› | 350 | 340 | 345 |
| 54 | ›› | 380 | 280 | 330 |
| 55 | ›› | 300 | 270 | 285 |
| 56 | ›› | 380 | 280 | 330 |
| 57 | ›› | 350 | 270 | 310 |
| 58 | ›› | 380 | 340 | 360 |
| 59 | ›› | 260 | 180 | 220 |
| 60 | ›› | 260 | 170 | 215 |
| 61 | ›› | 350 | 270 | 310 |
| 62 | ›› | 380 | 340 | 360 |
| 63 | ›› | 180 | 260 | 220 |
| 64 | ›› | 180 | 270 | 225 |
| 65 | ›› | 300 | 280 | 290 |
| 66 | ›› | 350 | 270 | 310 |
| 67 | ›› | 380 | 260 | 320 |
| 68 | ›› | 180 | 180 | 180 |
| 69 | ›› | 260 | 280 | 270 |
| 70 | ›› | 350 | 300 | 325 |
| 71 | ›› | 240 | 270 | 255 |
| 72 | ›› | 300 | 270 | 285 |
| 73 | ›› | 260 | 260 | 260 |
| 74 | ›› | 300 | 280 | 290 |
| 75 | ›› | 320 | 270 | 295 |
| 76 | ደራሽኛ | 180 | 180 | 180 |
| 77 | ›› | 410 | 270 | 340 |
| 78 | ›› | 240 | 240 | 240 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 79 | ›› | 180 | 240 | 210 |
| 80 | ›› | 210 | 270 | 240 |
| 81 | ›› | 240 | 270 | 255 |
| 82 | ›› | 320 | 260 | 290 |
| 83 | ›› | 300 | 270 | 285 |
| 84 | ›› | 350 | 270 | 310 |
| 85 | ›› | 260 | 280 | 270 |
| 86 | ›› | 350 | 260 | 305 |
| 87 | ›› | 320 | 180 | 250 |
| 88 | ›› | 300 | 300 | 300 |
| 89 | ›› | 320 | 340 | 330 |
| 90 | ›› | 210 | 280 | 245 |
| 91 | ›› | 240 | 340 | 290 |
| 92 | ›› | 300 | 270 | 285 |
| 93 | ›› | 320 | 280 | 300 |
| 94 | ›› | 180 | 270 | 225 |
| 95 | ›› | 210 | 260 | 235 |
| 96 | ›› | 350 | 270 | 310 |
| 97 | ›› | 300 | 160 | 230 |
| 98 | ›› | 260 | 280 | 270 |
| 99 | ›› | 260 | 160 | 210 |
| 100 | ›› | 300 | 260 | 280 |
| ድምር | | 30000 | 26410 | 28205 |
| መ. ልይይት | | 71.5202874 | 46.36471577 | 46.24318132 |
| አማካይ | | 300 | 264.1 | 282.05 |

## አባሪ አራት

### ሰንጠረዥ 4፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና አንድና ሁለት አጠቃላይ ውጤት

| | አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናዎች | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ፈተና1 | ፈተና 2 | አማካይ |
| 1 | ኦሮምኛ | 9 | 9 | 9 |
| 2 | ›› | 8 | 5 | 6.5 |
| 3 | ›› | 9 | 7 | 8 |
| 4 | ›› | 10 | 9 | 9.5 |
| 5 | ›› | 5 | 6 | 5.5 |
| 6 | ›› | 3 | 7 | 5 |
| 7 | ›› | 7 | 4 | 5.5 |
| 8 | ›› | 4 | 8 | 6 |
| 9 | ›› | 6 | 5 | 5.5 |
| 10 | ›› | 4 | 10 | 7 |
| 11 | ›› | 10 | 2 | 6 |
| 12 | ›› | 8 | 6 | 7 |
| 13 | ›› | 7 | 8 | 7.5 |
| 14 | ›› | 7 | 7 | 7 |
| 15 | ›› | 2 | 3 | 2.5 |
| 16 | ›› | 8 | 4 | 6 |
| 17 | ›› | 3 | 7 | 5 |
| 18 | ›› | 2 | 8 | 5 |
| 19 | ›› | 8 | 5 | 6.5 |
| 20 | ›› | 9 | 9 | 9 |
| 21 | ›› | 5 | 4 | 4.5 |
| 22 | ›› | 3 | 8 | 5.5 |
| 23 | ›› | 4 | 9 | 6.5 |
| 24 | ›› | 8 | 7 | 7.5 |
| 25 | ›› | 6 | 4 | 5 |
| 26 | ኮንሰኛ | 6 | 8 | 7 |
| 27 | ›› | 6 | 9 | 7.5 |
| 28 | ›› | 9 | 9 | 9 |
| 29 | ›› | 10 | 7 | 8.5 |
| 30 | ›› | 7 | 2 | 4.5 |
| 31 | ›› | 8 | 3 | 5.5 |
| 32 | ›› | 3 | 3 | 3 |
| 33 | ›› | 7 | 5 | 6 |
| 34 | ›› | 4 | 6 | 5 |
| 35 | ›› | 9 | 6 | 7.5 |
| 36 | ›› | 6 | 10 | 8 |
| 37 | ›› | 4 | 7 | 5.5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 38 | ›› | 4 | 4 | 4 |
| 39 | ›› | 8 | 5 | 6.5 |
| 40 | ›› | 5 | 5 | 5 |
| 41 | ›› | 5 | 6 | 5.5 |
| 42 | ›› | 8 | 4 | 6 |
| 43 | ›› | 9 | 8 | 8.5 |
| 44 | ›› | 4 | 7 | 5.5 |
| 45 | ›› | 8 | 4 | 6 |
| 46 | ›› | 4 | 7 | 5.5 |
| 47 | ›› | 8 | 6 | 7 |
| 48 | ›› | 7 | 8 | 7.5 |
| 49 | ›› | 8 | 7 | 7.5 |
| 50 | ›› | 6 | 7 | 6.5 |
| 51 | ደራሽኛ | 10 | 9 | 9.5 |
| 52 | ›› | 9 | 4 | 6.5 |
| 53 | ›› | 4 | 4 | 4 |
| 54 | ›› | 6 | 7 | 6.5 |
| 55 | ›› | 7 | 8 | 7.5 |
| 56 | ›› | 3 | 4 | 3.5 |
| 57 | ›› | 4 | 6 | 5 |
| 58 | ›› | 5 | 3 | 4 |
| 59 | ›› | 8 | 10 | 9 |
| 60 | ›› | 7 | 9 | 8 |
| 61 | ›› | 4 | 8 | 6 |
| 62 | ›› | 3 | 3 | 3 |
| 63 | ›› | 9 | 6 | 7.5 |
| 64 | ›› | 10 | 9 | 9.5 |
| 65 | ›› | 9 | 7 | 8 |
| 66 | ›› | 6 | 6 | 6 |
| 67 | ›› | 2 | 6 | 4 |
| 68 | ›› | 9 | 10 | 9.5 |
| 69 | ›› | 8 | 8 | 8 |
| 70 | ›› | 5 | 3 | 4 |
| 71 | ›› | 7 | 7 | 7 |
| 72 | ›› | 8 | 5 | 6.5 |
| 73 | ›› | 7 | 6 | 6.5 |
| 74 | ›› | 4 | 5 | 4.5 |
| 75 | ›› | 6 | 6 | 6 |
| 76 | ኮረቴ | 10 | 9 | 9.5 |
| 77 | ›› | 2 | 6 | 4 |
| 78 | ›› | 5 | 8 | 6.5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 79 | ›› | 10 | 8 | 9 |
| 80 | ›› | 7 | 3 | 5 |
| 81 | ›› | 6 | 3 | 4.5 |
| 82 | ›› | 4 | 4 | 4 |
| 83 | ›› | 4 | 4 | 4 |
| 84 | ›› | 3 | 3 | 3 |
| 85 | ›› | 6 | 6 | 6 |
| 86 | ›› | 4 | 7 | 5.5 |
| 87 | ›› | 3 | 8 | 5.5 |
| 88 | ›› | 3 | 7 | 5 |
| 89 | ›› | 3 | 4 | 3.5 |
| 90 | ›› | 8 | 6 | 7 |
| 91 | ›› | 5 | 3 | 4 |
| 92 | ›› | 4 | 6 | 5 |
| 93 | ›› | 4 | 6 | 5 |
| 94 | ›› | 9 | 4 | 6.5 |
| 95 | ›› | 7 | 4 | 5.5 |
| 96 | ›› | 2 | 5 | 3.5 |
| 97 | ›› | 5 | 10 | 7.5 |
| 98 | ›› | 5 | 6 | 5.5 |
| 99 | ›› | 6 | 9 | 7.5 |
| 100 | ›› | 3 | 9 | 6 |
| **ድምር** | | 606 | 621 | 613.5 |
| **አማካይ** | | 6.06 | 6.21 | 6.135 |
| **መ.ልይይት** | | 2.334718 | 2.114381 | 1.708742 |

## አባሪ አምስት

### ቃለ መጠይቅ ለመምህራን

በ2010 ዓ.ም በሰገን 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እያስተማሩ ከሚገኙ መምህራን ጋር የሚደረግ ቃለመጠይቅ

### ዝርዝር ጥቄዎች

1. በአጠቃላይ ሲታይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው-----------------------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
2. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆነ ይህ ችግር ከምን የመጨ ይመስልዎታል-----------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
3. ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ያውቋቸዋል----------------------
4. ከፈጣንና ከዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው-----------------------------------------------------------------------------------------------
5. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንባብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት ባለ ዘዴ ነው----------------------------------------------------------------------------------------------
6. የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ስራዎች አሉ-------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
7. ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምንያህል ነው-----------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
8. የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የንበብ ፍጥነት ለማዳበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ-------------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------
9. በመጨረሻም ተጨማሪ አስተያየት ካሎት ይግለጹ------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------------------------------------------------

**ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ላደረጉልኝ መልካም ትብብር ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ!!**

**ለመምህራን ከቀረበ ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ**

***<u>መምህር አንድ</u>***

ጥያቄ 1- በአጠቃላይ ሲታይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው?

መልስ፡ እንኳን አንብቦ መረዳት ይቅርና ፊደልን የማይለዩ ተማሪዎች ሁሉ አሉ፡፡ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንደ ትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ትልቅ ችግር እንደሆነ አምናለሁ፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎቹ ከፍተኛ የንባብ ችግር አለባቸው ከጥቂት በጣት ከሚቆጠሩ ተማሪዎች በስተቀር፤

ጥያቄ 2፡ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆነ ይህ ችግር ከምን የመነጨ ይመስሎታል?

መልስ፡ በቅድመ መደበኛ እና በታችኞቹ የክፍል ደረጃ ላይ በትኩረት አልተሰራም ተማሪው የሚጠበቅበትን ችሎታ ሳይዝ ሁለተኛ ደረጃ ይመጣል፡፡ ለማስተማር ትልቅ እንቅፋት ይሆናል፡፡ የማንበብ ልምድ አለመኖርም ሌላው ችግር ነው፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋም ተጽእኖው ቀላል አይደለም፡፡ አማርኛ ኢንተራንስ ላይ ስለሌለ ተማሪው ብዙም ትኩረት አይሰጠውም፡፡

ጥያቄ 3፡ ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ያውቋቸዋል?

መልስ፡ ከዚህ ቀደም ይህንን ሁኔታ አላስተዋልኩትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንድ ስልጠና ከወሰድኩ በኋላ የተማሪዎችን የንባብ ፍጥነት ለመለካት ሞክሬ ነበር፡፡ በዚህም ፈጣን አንባቢዎች በደቂቃ እስከ 121 ቃላት እንደሚያነቡ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በዚህም የፈጣንና የዝግተኛ አንባቢዎችን የአንብቦ መረዳት ስለካ ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው ማወቅ ችያለሁ፡፡

ጥያቄ 4፡ ከፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

መልስ፡ ፈጣን አንባቢዎች ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላቸው፡፡

ጥያቄ 5፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንባብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት ባለ ዘዴ ነው ?

መልስ፡ ተማሪዎቹ መጀመሪያ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ካደረግኩ በኋላ እኔ ደግሞ መልሼ አነበዋለሁ፡፡ ይህንን የማደርገው ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲያነቡ ምንባቡን በትክክል ማንበባቸውን፣ ተገቢ አገላለጽ መጠቀማቸውን፣ ስርዓተ ነጥቦችን ወዘተ በአግባቡ ማንበባቸውን ለመከታተል እና ተማሪዎቹ ሲሳሳቱ ለማረም እና ለተማሪው ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ነው፡፡

ጥያቄ 6 ፡ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ስራዎች አሉ?

መልስ፡ ቅድም እንደገለጽኩት የተማሪዎችን የማንበብ ፍጥነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተወሰነ መንገድ ለመለካት ሞክሬአለሁ፤ ነገር ግን ለውጥ ሊያመጣ በሚችልና መፍትሔ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ የተሰሩ ስራዎች የሉም ቢባል የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡

ጥያቄ 7፡ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው?

መልስ፡ ተማሪው የንባብ ፍጥነቱንም ሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታውን ለማዳበር ጥረት ሲያደርግ አይስተዋልም፡፡ መምህራኑ ተማሪዎቹ የተለያዩ ምንባቦችን እንዲያነቡ አይገፋፉዋቸውም፡፡

ጥያቄ 8፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

መልስ፡ ለአማርኛ ቋንቋ ትኩረት ቢሰጠው ቢያንስ ኢንትራንስ ላይ ቢኖር፣ ክፍለ ጊዜው በቂ አይደለም መስተካከል አለበት ተማሪውም ከቴክኖሎጂ ጋር አብሮ እንዲሄድ ማንበብ እንዳለበት መምከር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

ጥያቄ 9፡ ተጨማሪ አስተያየት ካሎት ይግለጹ?

መልስ፡ በተለይ ንባብን በተመለከተ ሀገራዊ ችግር እየሆነ የመጣበት ሁኔታ ስላለ ሁሉም አካል ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ፣ ለመምህሩም ንባብን በተመለከተ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ቢሰጥ የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

__መምህር ሁለት__

ጥያቄ 1- በአጠቃላይ ሲታይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው?

መልስ፡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም በክፍል ውስጥ ምንባቡ እንዲያነቡ ሲደረጉ ፈቃደኛ የማይሆኑ ተማሪዎች ገጥመውኛል፡፡ ከዚህ የተረዳሁት ዝቅተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳላቸው ነው፡፡

ጥያቄ 2፡ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆነ ይህ ችግር ከምን የመነጨ ይመስሎታል?

መልስ፡ ሳያጣሩ ከክፍል ክፍል ይሸጋገራሉ ተማሪው በደንብ መያዝ ያለበት በአንደኛ ደረጃ ነው በተጨማሪም የክፍለ ጊዜ እጥረት እያንዳንዱን ተማሪ እንኳን ለመለካት የተሰጠ የቤት ስራን እንኳን ለማረም በቂ አይደለም፡፡ ተማሪው ከማንበብ የተለያዩ ፊልሞችን፣ የቃና ፕሮግራምን ይከታተላል ይህም ተጽእኖ አሳድሯል፡፡

ጥያቄ 3፡ ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ያውቋቸዋል?

መልስ፡ እነዚህን ተማሪዎች ለይቶ ለማወቅ የተደረገ ጥረት የለም፡፡ አሁን ላይ ፈጣን አንባቢ ከዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ የመረዳት አቅም አለው ለማለት ቢከብድም ካለው እውነታ እና የማስተማር ልምድ ፈጣን አንባቢዎች ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ አንድን ምንባብ አንብበው ይረዳሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

ጥያቄ 4፡ ከፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

መልስ ፡ ከዝግተኛ አንባቢዎች ይልቅ ፈጣን አንባቢዎች ቶሎ አንብበው የመረዳት ችሎታ አላቸው፡፡

ጥያቄ 5፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንባብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት ባለ ዘዴ ነው ?

መልስ፡ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት የሚሰጠው በለሆሳስ ነው፡፡ ማለትም ተማሪው ድምጹን ሳያሰማ የሚያነብ ከሆነ ለአድማጭ ስለማይጨነቅ ትኩረቱ በምንባቡ መልእክት ላይ ብቻ ስለሆነ የተሰጠውን ምንባብ የመረዳት ችሎታው ከፍተኛ ይሆናል በዚያው መጠን ፍጥነቱም ይጨምራል፡፡

ጥያቄ 6 ፡ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ስራዎች አሉ?

መልስ፡ እንግዲህ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚለካው በየምዕራፉ ያሉ ምንባቦችን ተማሪዎች ካነበቡ በኋላ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ይደረጋል ከዚህ የዘለለ ነገር የለም፡፡

ጥያቄ 7፡ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው?

መልስ፡ ተማሪዎቹ እንኳን ሌሎች መጽሐፍቶችን ማንበብ ይቅርና የራሳቸውን መጽሐፍ አንብበው እንዲመጡ ሲታዘዙ ከጥቂት ተማሪዎች በስተቀር አብዛኛው ተማሪ አንብቦ አይመጣም በመሆኑም የንባብ ፍጥነታቸውም ሆነ የንባብ ልምዳቸው ዝቅተኛ ነው፡፡

ጥያቄ 8፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

መልስ፡ ዋናው ጉዳይ ከታችኞቹ ክፍል ጀምሮ የንባብ ችሎታቸውንና ደረጃውን እያሟላ እንዲመጣ ቢደረግ፣ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን እየቀያየሩ የማስተማር ልምድ እንዲኖር ስልጠናዎች ቢሰጡ መምህሩም የተማሪዎችን ክፍተት ለመሙላት ቢሰራ ጥሩ ነው፡፡

ጥያቄ 9፡ ተጨማሪ አስተያየት ካሎት ይግለጹ?

መልስ፡ እላይ የጠቀስኳቸው አስተያቶች ተግባራዊ ቢሆኑ ለውጥ ይመጣል የሚል እምነት አለኝ፡፡

## መምህር ሶስት

ጥያቄ 1- በአጠቃላይ ሲታይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ያህል ነው?

መልስ፡ ንባብ ለቋንቋ ትምህርት እና ለሌሎችም የትምህርት አይነቶች አስፈላጊ እና ወሳኝ ክሂል ቢሆንም የተማሪዎች የንባብ ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ተገንዝቤአለሁ፡፡

ጥያቄ 2፡ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው የሚሉ ከሆነ ይህ ችግር ከምን የመነጨ ይመስሎታል?

መልስ፡ አንደኛ ተማሪዎቹ ከታችኛው ክፍል ጀምረው በትክክል ፊደል ለይተው በየክፍል ደረጃቸው ማንበብ የሚገባቸውን አንብበው እና በቂ የሆነ የንባብ ችሎታ ሳይዙ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ይመጣሉ፡፡ በሌላ አገላለጽ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ይመጣሉ፡፡ ሌላው ተማሪው በራሱ የንባብ ችሎታችን ለማዳበር ጥረት አያደርግም፡፡ ከተማሪው ብዛት የተነሳ መምህሩም በሚገባ አይከታተልም፡፡ በእኔ አመለካከት እነዚህ ችግሮች በተማሪው ንባብ ላይ ተጽእኖ አሳድሯል እላለሁ፡፡

ጥያቄ 3፡ ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለይተው ያውቋቸዋል?

መልስ፡ ፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎችን ለመለየት የተለየ የሰራሁት ስራ ባይኖርም ከልምድ እንዲሁም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚተገብሩት በመነሳት ፈጣን አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት አቅም ይኖራቸዋል ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡

ጥያቄ 4፡ ከፈጣንና ዝግተኛ አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

መልስ፡ ፈጣን አንባቢዎች የተሻለ አንብቦ የመረዳት አቅም አላቸው፡፡

ጥያቄ 5፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንባብ ልምምድ የሚያደርጉት እንዴት ባለ ዘዴ ነው ?

መልስ ፡ እንግዲህ የተለያዩ ምሁራን እንደገለጹት ተማሪዎች አንድን ምንባብ አንብበው መልእክቱን የሚረዱት በዝምታ ሲያነቡ ነው ስለሚሉ በፍጥነት አንብቦ ለመረዳት

ጠቃሚ ነው ተብሎ በጥናቱ የተረጋገጠው የጮክታ ንባብ ሳይሆን የዝምታ ንባብ ስለሆነ በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የማደርገው ይህንን ስልት ነው፡፡

ጥያቄ 6 ፡ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማወቅ በግል ወይም በትምህርት ቤት ደረጃ የተሰሩ ስራዎች አሉ?

መልስ፡ እንደትምህርት ቤት በማጠቃለያ ፈተና ላይ የንባብ ጥያቄ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ በክፍል ውስጥ ደግሞ በመጽሐፍ ላይ ያሉትን የምንባብ ጥያቄ እንዲሰሩ ነው የምናደርገው ከዚህ ውጪ በጥናት የተደገፈ ስራ አልተሰራም፡፡

ጥያቄ 7፡ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውንና የንባብ ፍጥነታቸውን ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው?

መልስ፡ ብዙም ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም ምንአልባት ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው ትኩረት አነስተኛ ስለሆነ ይመስለኛል ወይም የንባብ ልምድ አለመኖር ይሆናል፡፡

ጥያቄ 8፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እና የንባብ ፍጥነት ለማዳበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

መልስ፡ ተማሪው አንደኛ ደረጃ ጨርሶ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሲሸጋገር በቂ የሆነ የንባብ ችሎታ ይዞ እንዲመጣ ቢደረግ፣ ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸውን የሚያዳብሩበት ሁኔታ ቢመቻች እና ተገቢው ድጋፍ ቢደረግላቸው እንዲሁም ለቋንቋ ትምህርቱ ትኩረት ቢሰጠው የተሻለ ነገር ይፈጠራል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

ጥያቄ 9፡ ተጨማሪ አስተያየት ካሎት ይግለጹ?

መልስ፡ አጽንኦት የሚሰጠው የመምህራንን ብቃት ለማሳደግ የተለያዩ ስልጠናዎች ቢሰጡ፣ መጽሐፍ ሲዘጋጅ የተለያዩ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን የሚለኩ ሆነው ቢዘጋጁ፣ ክፍለ ጊዜው ማስተካከያ ቢደረግ እላለሁ፡፡

# ማረጋገጫ

ከታች ስሜና ፊርማዬ የተጠቀሰው ተማሪ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ ስራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥም የተጠቀምኳቸውን ዋቢዎች በሙሉ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ተማሪ ________________________________

ፊርማ ________________________________

ቀን ________________________________